# ቤተክርስትያን እና ሁኔታዋ

ዛሬ ጠዋት ባልተለመደ በሽታ ለተያዘች ህጻን በተለየ መልኩ እንጸልያለን፡ ሁላችንም ይሄን ማድረግ አለብን። ሐኪሞቹ እንኳን አላወቁትም። ብቻ የሆነ ስም ሰጥተውታል፤ እንደኔ ግን—ተስማምተው ሰጡት እንጂ፤ ምንነቱን ያወቁት አይመስለኝም። ክርስቶስ ግን፡ ምን መሆኑ ያውቃል። እኔም ልነግራችሁ እችላለሁ፤ ዲያቢሎስ ነው፤ ልክ ነው፤ ዲያቢሎስ ነው። ማን ይበሉት፤ ለምን፤ እነርሱን ይመለከታል። እሱ ግን እንዲያ ነው፡ እያችሁ፡ ክፉ መንፈስ ነው። አሁን፡ ሁላችንም በአንድ ላይ፡ በሕብረት፤ ሁሉም ሰው እኩል፤ **እመን ብቻ** እንዘምር።

> እመን ብቻ፡ እመን ብቻ፣
> የማይቻል የለም፡ እመን ብቻ፤
> እመን ብቻ፡ እመን ብቻ፣
> ሁሉ ይቻላል፡ እመን ብቻ...

2 እህቴ፤ ጌታ ይፈውሰሻል። አንገታችንን ደፍተን ለልጅቷ አሁን እንጸልይ።

3 የሰማይ አባታችን፤ እኔ ከሐሳቤ ማውጣት ተስኖኛል። ይህች ብላቴና፣ በሞት አፋፍ ናት፣ ደግሞም የአንድ ሰው ውድ ነች። ፍጥረትህም ናት፤ ሰይጣንም ጨቅላ ሕይወቷን እየቀጠፈባት ነው። በክርስቶስ ስም የሞትን እጅ እንድትመልስ፣ ጠላትንም እንድታባርረው እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፤ አንተ'ኮ ቀይ ባሕርን በሁለቱም ወገን አቁመህ፤ ለእስራኤል ልጆች፣ ርስትህን፤ ወደ ተስፋይቱም ምድር የሰላም መንገድ ሰጥተሃቸዋል። እግዚአብሔር ሆይ፤ እንቅፋቶችን ሁሉ አስወግደህ ህጻኗን እንድታቆያት እንጸልያለን። እንድንጠይቅ ተሰጥቶናልና። እናም፤ በአንተ እንደሚያምኑ ሰዎች፤ የህጻኗን መፈውስ በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

4 ዛሬ እኔ በጌታ በኢየሱስ ስም እንደገና በምስጋና በተሞላ ልብ—ወደ እናንተ መጥቻለሁ። ምናልባት ከእሁድ በፊት እዚህ ከደረስኩ የሰንበት ትምህርት እካፈላልሁ ብየ አስቤ፤ ከሉዊዚያና ቀደም ብዬ ነው ቤት የደረስኩት። ያኔ እዚያ የአየሩ ሁኔታ እጅግ ሞቃታማ ነበር፤ እኛ... ሊዊዚያና ይልቅ፤ ይህ ማለዳ የተሻለ፣ ረጋ ይላል። በሉዊዚያና ውስጥ ካለ ማቀዝቀዣ በእንደዚህ ዓይነት ሕንፃ ውስጥ በጭራሽ አትቀመጡም፣ በማቀዝቀዣ ይቀዘቅዛል ወይም ስታችሁ ትወድቃላችሁ።

5 እናም እኔ የመጣሁት ወዲያውኑ ከመሄዴ በፊት የአንድ-ወይም-የሁለት ቀን ዕረፍትን ብቻ ባገኝ በማለት ነው፣ በሚቀጥለው ሳምንት፤ ልዑል አልበርት ወደላበት፤ ወደ ሰሜናዊ ሳስካቼዋን ከመሄዴ በፊት። ይህ ማለት ከዳር እስከ ዳር፤ የዓለም ሁሉ መንገዶች እንደመጓዝ ነው። ምንም መንገድ ሳያስቀር ዓለም ዙሪያ ሁሉ ያካልላል፤ ይህ በዚህ ጊዜ የምንሄድበት ከሕንዳውያን እና ከእስክሞሶች በቀር ሌላ የሌለበት ወደ ውስጥ ራቅ ያለ ነው። ስለዚህ በዚህ ስብሰባ ላይ ከመላው ካናዳ የመጡ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ። ከእነሱ መካከል አንዳንዶቹ ከዌስት ኮስት ይወርዳሉ፤ እንመጣለን፤ ብሏል። እናም እናንተ

እንድትጸልዩልን አብዝተን የምንሻው እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንድንገናኝ አብዝቶና፤ አትረፍርፎ፤ ስለክብሩም የሆነ ታላቅ ጉባኤ እንዲሰጠን ነው። ካናዳ ከሄድኩ አራት ወይም አምስት አመት ሆኖኛል። እዚያም ጥቂት እውነተኛ ንጉሣውያን ጓደኞች አሉኝ፤ በጣም ጥሩ ሰዎች ናቸው።

6 እናም ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄዱ በጣም ታማኝ ናቸው። ምንም ያህል ቢቀዘቅዝ፤ ብርድ ልብስን ጠምጠም አድርገው እና ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድ፤ በበረዶ ጋሪ ላይ ቁጭ ብለው በፈረስ ሰላሳ ማይል ይጓዛሉ። ወጣት እና አዛውንት በበረዶ መሰናክሎች እና ሌሎችም ሁሉ ውስጥ፤ ይሄዳሉ። ሁሉም አንድ ላይ ይሰበሰባሉ። አንዱ ቤተሰብ ከሌላው ጋር ተገንኝተው ጉዞ ይጀምራሉ፤ እና ይሄዳሉ። ከአገልግሎቱ ብዙ እንዲባረኩ የሚያደርጋቸው ያንን—የሚከፍሉት ዋጋ ነው። ዋጋ በማይከፈልበት ጉባኤ፤ ብዙ በረከት አይገኝበትም። አንዳች እናንተ የምትጎድሉበት ኪሳራ በማድረግ እጅግ ዝቅ ማለት አለባችሁ፣ አንድን ነገር ወደ ጎን ትታችሁ፤ እግዚአብሄርን እንደምትወዱት ለማሳየት ቤተክርስትያን ስትሄዱ፤ **ያንን** እና **ይሄንን** ስራ አቁማችሁ፤ ለመሄድ ዋጋ ትከፍላላችሁ፤ ያኔ ነው አንዳች ነገር የምታገኙበት።

7 ልክ እንደ ልጆቼ ነው። ቢሊ ፖል፤ እኔ ሳስብ... እኔ በልጅነቴ ምንም አላገኘሁም። እማማ ምናልባት አንድ እሽግ ከረሜላ ስታገኝ፤ ለእያንዳንዱ ሁለት ወይም ሦስት በቁጥር ታከፋፍለን ነበር። ምናልባት ለገና ትንሽ የቆርቆሮ ጥሩምባ ወይም ትንሽ ቆብ ሽጉጥ፣ ወይም የሆነ ነገር እናገኝ ይሆናል። ሌሎች ልጆች ተንሸራታች እና ብስክሌቶችን እና ነገሮችን፤ ጥሩ ልብሶችን እና ሞቅ ካለ ጃኬቶች ጋር አይቻለሁ። እና—እኔን፤ እጅግ በጣም ያሳዝነኛና፤ እንዲህ እላለሁ፤ "የራሴ ልጆች ሲኖሩኝ፤ የምችለውን ሁሉ ለእነሱ አደርጋለሁ።" አዎን፣ ለልጆቼ አንዳች ነገር ለማግኘት ሰል ለመራብ ፈቃደኛ ነኝ። እና እኔ ሰኖር... ቢሊ ገና ትንሽ ልጅ በነበረበት ጊዜ፤ ትንሽ ባለሶስት ጎማ ብስክሌትና፤ ሁሉንም ነገር አመጣለት ነበር። ሜዳም ለሱ የሆነ ነገር ለማድረግ፤ ሁሉንም ነገር ትሞክራለች፤ የራሷን ልብስ እና ነገሮች መሥዋዕት ታደርጋለች። ምን መረዳት እንደጀመርን ግን ታውቃላችሁ? ባለ ሶስት እግር ብስክሌት፣ ትንሽየ ቀስት እና ፍላጻ፣ እና ሌሎችም ነገሮች አምጥቼለት። ትንሽ ማንኪያ እና እንጨት ነገር፤ ይይዝና—በጓሮው፤ የሆነ ጥግ ላይ ይቆፍራል። አያችሁ? እንዲህ አልኩኝ፤ "ቀጣዮቹ እንኳን እንደዚያ አይሆኑም።" አያችሁ? ለማንም ማንኛውንም ነገር በእጃቸው ላይ ሰጡአቸው፣ እነሱ አይፈልጉትም። እንዲሁ መሰዋዕት ማድረግ የሚገቡ ነገሮች ናቸው!

8 የመዳን መንገድም እንዲሁ ነው። ሙሉ መሰዋዕት ነው። ነው፤ ወንድም ሮይ። ዘወትር መተግበር የሚገባችሁ መሰዋዕትነት—ነው፣ የሆነ ነገር—ወደ እግዚአብሄር የሚያሰቀርባችሁ ነገር ማድረግ ነው። እና ዛሬ ጠዋት በዚህ ሞቃት ሕንፃ ውስጥ ስትቀመጡ፤ ለሁላችሁ መሰዋዕት መሆኑን አውቃለሁ። እዚህ ቁጭ ባልንበትም፤ ሐሳባችን ሁሉ የሰው ልጅ እንዲፈጽመው በተሰጠው ታላቁ መሥዋዕት ላይ እናድርግ፣ ይህም ስለ እኛ እንዲሞት ወደ ምድር እንዲመጣ የታዘዘው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ያ ብቻ አይደለም፣ ነፍሱ ወደ ሲኦል ወርዳ ለሦስት ቀናት እና ለሊት እዚያ ነበረች፣ በሦስተኛውም ቀን ተነሣ፣ አሁን በሰማይ፤ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ፤ ወደ ላይ ዐርጓል፤ ለእኛ በተሰጠ ጸጋው እና ማስተሰርያው ላይ ባለን እምነት ላይ እያስታረቀ ይገኛል።

9 አሁን በዚህ... በዚህ በምንሄድበት ሰፍራ፤ እጅግ ድሀ፣ በጣም ድሀ፤ የሆኑ ሰዎች አሉ፤ ወደ ሰብሰባው ለመምጣት፤ ላሞቻቸውን፣ ሁለት ወይም ሶስት በጎች፣ ወይም ሌላ ነገር ይሸጣሉ። ሸማግሌ እስኪሞ ምናልባት አንዳንድ ቆዳዎቹን አምጥቶ ይሸጣል፣ ያም ደግሞ ቤተሰቡ እንዲወጡ እጅግ የሚጠቅመው ነው። የህንድ ነጋዴው እንዲሁ ማድረግ ይኖርበታል። አሁን፣ ቢያንስ ለእነዚያ ሰዎች መጸለይ እንችላለን፣ አይደል? እናም እግዚአብሔር ታላቅ ነገር እንዲሰጣቸው እንጸልያለን።

10 አሁን፣ ሞቃት ስለሆነ፣ ረጅም ላቆያችሁ አልፈልግም። ለታመሙ ሰዎችና፣ **ለቤተክርስቲያን እና ሁኔታዋ** ጸሎት ከማድረጋችን በፊት፣ ዛሬ ጠዋት ሐሳባችን ሰብሰብ እንድናደርግ እፈልጋለሁ። እናም፣ አሁን፣ ከጥቂት ቀናት በፊት ለቤተክርስቲያን መልእክት እንደተሰጠኝ ይሰማኛል በሼርቪፖርት፡ ልዊዝያና፤ የቤተክርስትያን ሁኔታዎች በተመለከት—እንደሆነ አምናለሁ። ስለዚ ዛሬ ጠዋት በዚህ ጉዳይ ጌታን እንሞግታለን፤ ጌታ እንዲረዳን እንጸልያለን ደግሞም እንጠይቃለን። ተመሳሳዩን አካሄድ ለመጠቀም አታቅዱ፣ በምንኖርበት በዚህ ቀን ጌታ እንዲረዳን ግን ጠይቁ። እና አሰቀድመን... ታላቁ ጥንታዊው መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ነው፤ በዚያ ውስጥ ግን የዘላለም ሕይወት ይዘቶች አሉ።

11 ቃል እግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔርም ከቃሉ በላይ እንዳይደለ፤ ይህን አስታውሱ። እኛም ይህን ብናደርግ... ከቃላችን በላይ አይደለንም። በርግጥ፡ አሁን፡ እኔም እናንተም በተለያየ አስተሳሰብ... አቋም፤ ሁላችንም "ኦ፤ እኔ ይሄን አደርጋለሁ" ልንል—እንችላለን፤ ከልባችንም ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ይሄን አደርጋለሁ ያልናቸውን ነገሮች እንዳናደርግ—ሁኔታዎች ሊነሱ ይችላሉ። እግዚአብሔር ግን ሁሉን ነገር፣ የነበረው እና፣ የሚመጣውን ሁሉ የሚያውቅና፤ ፍጻሜ የሌለው ሰለሆነ፤ እንዲህ አያደርግም፤ ወይም... ስለዚህ፤ እንደሚፈጽመው እርግጠኛ ሳይሆን፤ አንዳች ሐሳብ አይናገርም።

12 አብርሃምም፣ መቶ ዓመት ሲሆነው፤ ያልነበሩትን ነገሮች፤ እንደነበሩ አድርጎ ቆጠራቸው። አሁን የምናገራቸው ነግሮች ለታመሙና ለሚጸለይላቸው ሰዎች፤ እንደ መጽናኛ ናቸው። አብርሃምም ያልነበሩትን ነገሮች፤ እንደነበሩት አድርጎ ቆጠረ፤ ያን ቃል የገባለት የገባለትን ቃል እንዲፈጽም አድርጎ በመቁጠር፤ ወይም፤ የገባውን ቃል እንደሚጠብቅ አሰበ። አሁን፤ እግዚአብሄር ሲነግረው፤ አብራሃም የሰድሰት... ሰባ-አምሰት፤ ሳራህ ስድሳ-አምሰት ሆነው፤ ልጅ እንደሚወልዱ ነገራቸው፤ ለምን፤ በአጠቃላይ የማይቻል ነበር። እሱ ግን አመነው እና ልጅን መጠባበቅ ጀመረ፤ ልጁ ህያው እንደሆነ አድርጎ ቆጠሮ፤ ይህም ልጁ ሳይመጣ ከሀያ-አምሰት አመታት በፊት ነው። እሱ ግን ሰላመነ፤ ሕፃኑ በተወለደ ጊዜ አብራሃም መቶ ነበር፤ ሣራም ዘጠና ነበረች። የሌሉን ነግሮች እንዳሉ አድርጎ፤ ቆርጦ ነበርና።

13 አሁን፤ ይህ ሊጸለይላቸው ለተዘጋጁ ለታመሙ እና ለተጠቁቱ ነው። ችግሮቻችሁ ምንም ቢሆኑ፤ አንድም እንዲህ ብትሆኑ... ምንም በሽታ ይኑራችሁ፣ ምንምም ክፉ ብትሆኑ፣ ክርስቶስን ስትቀበሉ፤ ቃሉን ስትቀበሉ፤ ያኔ አሁን ያሉ ነገሮች እንዳልነበሩ ትቆጥራላችሁ፤ የእግዚአብሄርን ቃል የሚጻረሩ ከሆኑ። አሁን፤ እግዚአብሄር ሲናገር፤ "የእምነት ጸሎት ህመምተኛውን ትፈውሳለች ብሏል።" እንግዲህ፡ ጌታ ከተናገረ ይህ ያረጋጋዋል። ከዚያ አእምሯችንን፣

ተስፋችንን እናስቀምጥ እና እንደ ተከናወነ አድርገን እንሥራ። እኛ ስንቀበለው ቀድሞውኑ ጨርሶታል።

14 መዳንም እንዲሁ ነው። እናምናለን፣ እንቀበለዋለን፣ በልባችን እናምነዋለን፣ በእግዚ አብሄር ፊት ቀርበን ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ እንቀበላለን፤ እሱን እንቀበለዋለን። በዚህ ማለዳ፤ ያልዳነ፣ ሐጥያተኛ ሆነህ፣ መፈወስ የምትፈልግ፣ ህመምተኛ ነህ፤ አስቀድመህ ጌታ ፈልገው። እንደ መድሐኒት ተቀበለው፤ ከዛ በኋላ ሕመሙ ወድያው ይለቃል። ምንም ነገር ቢሆን፤ (የአቅማችሁን ሁሉ) ሐሳባችሁ ሁሉ፤ ሙሉ በሆነው ሰው፤ በክርስቶስ ኢየሱስ አኑሩት፤ ሌላው ሁሉ መልካም ይሆናል።

15 ስለዚህ አሁን ሐሳባችሁ በዚሁ ላይ አኑሩትል፤ እነዚህ የነገርኳችሁ ጥቂት ቃላት ለታመሙ እና ለተጠቁት ሰዎች ናቸውና፤ ስለዚህ ዛሬ ጠዋት ለቤተክርስቲያን እና ሁኔታዋ እናገራለሁ። መለኮታዊ ፈውስ አስደናቂ ቢሆንም፤ ይሄም ተሰምቶኛልና። ሽሬቬፖርት ውስጥ በነበርኩ ጊዜ ግን፤ እዚያ ሳለሁ ሦስት የፈውስ አገልግሎቶች ብቻ ነው ያካሄድኩት፤ ከአስራ አንድ ቀናት ውስጥ፤ ሶስት፣ ወይም ምናልባት አራት። በመለኮታዊ ፈውስ ላይ ብዙ ጊዜ ከማጥፋት ይልቅ ለሰዎች ነፍስ መስበክ በጣም አስፈላጊ ነው። ምንም እንኳን፣ የታመሙና የተቸገሩ ሰዎች፣ እግዚአብሔር ሊፈውሳቸው ቢችልም። እንደሚፈውሰም፤ በመላው ዓለም እራሱን አረጋግጧል። አሁን ግን ዋናው ቁምነገር፤ ፈጽማ ስለማትሞተው፤ ነፍስ ነው። ስጋ ይሞታል። ነፍስ ግን በጭራሽ አትሞትም፣ እናም ያንን ደረጃ እያስጠበቅን ከእግዚአብሔር ጋር ቅን መሆን አለብን።

16 እኔ ብዙ ጊዜ ይህንን ተናግሬያለሁ። በዚያች ማለዳ ወንዙ ድረስ ስመጣ፤ ምንም እንቅፋት አልፈልግም፤ ሁሉ ቦታ ቦታውን እንዲይዝልኝ እፈልጋለሁ። ስሜን እየጠበቅኩ፤ ትኬቴን ብእጄ መያዝ እፈልጋለሁ። ወንድም ክሪች፡ እኔም እንደ ጥንቱ፡ ጳውሎስ እንደተናገረ "በትንሳኤው ሐይል አውቀዋለሁ" እንድል እፈልጋለሁ። ይህም ከሙታን መካከል በተጣራ ጊዜ፤ እንድወጣ... በትንሳኤው ሐይልም እንዳውቀው ነው።

17 ስለዚህ፤ አሁን፤ የመጽሀፉ ደራሲ ፊት፤ ለትንሽ ደቂቃ ልባችን እና ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

18 አባታችን፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ቃልህን እንድትገልጥልን፡ አንተን ለመጠየቅ፤ አሁን ወደ አንተ መጥተናል። እኛ ገጾችን መክፈት ብቻ እንችላለን፡ መንፈስ ቅዱስ ግን ቃሉን ይገልጣል። ስለዚህ አባት ሆይ፤ በዚህ ማለዳ ለእኛ ገልጠህ፡ ተርፎ ከሚፈስው ጸጋህ ሰጠን። አንተኑን እንተብቃለን። መንፈስ ቅዱስ ቃሉ ውስጥ ገብተህ ለሰው ልብ በሰው አንደበት ተናገር፡ እንደየመሻታችንም በእያንዳንዳችን ልብ ያኑርልን። ጉባኤው ሲያልቅም፤ ወደየቤቶቻችን ለመሄድ ተዘጋጅተናል፤ እራሶቻችን በትሕትና ዝቅ በማድረግ ክብር እና ምስጋናም እንሰጥሀለን፤ ስላደረግክልን ሁሉ እና ከአንተ ስለተማርነው ሁሉ። በክርስቶስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

19 የቃሉ ንባብ፡ በቅዱስ ዮሃንስ፡ 1ኛው ምዕራፍ፤ አብራችሁኝ ማንበብ ለምትፈልጉ እና መጽሃፍ ቅዱስ ለያዛችሁ ወይም ማስታወሻ መያዝ ለፈለጋችሁ። ጽሑፉን ከቃሉ እናነበዋለን፤ ከዛ በኋላ እንጸልያለን፤ መንፈስ ቅዱስም ጽሑፉን ከቃሉ ላይ ወስዶ ይሰጠናል። ልናነበው እንችላለን፣ ማንበብ

የሚችል ሁሉ ሊያነበው ይችላል፤ ትርጉሙ ግን እግዚአብሔር ብቻ ያወጣዋል። ቃሉ ስለሆነ፡ ጽሑፉን ማንበብ ይቻላል፡ ነገር ግን—ትርጉሙ ከእግዚአብሔር መሰጠት አለበት። አሁን፡ በቅዱስ ዮሃንስ፡ 1ኛው ምዕራፍ፡ ከ 28ኛው ቁጥር ተነስተን፡ እስከ ቁጥር 32 ድረስ እናነባለን።

> **ይህ ነገር ዮሐንስ ያጠምቅበት በነበረው... ?... በዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ በቤተ ራባ ሆነ።**
>
> **... በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ፡ እንዲህ** አለ፡ **እነሆ የዓለምን** ኃጢአት **የሚያሰወግድ የእግዚአብሔር በግ።**
>
> **አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል፥ ከእኔም በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል ብዬ ስለ እርሱ ያልሁት ይህ ነው።**
>
> **እኔም አላውቀውም ነበር፥ ዳሩ ግን... ለእስራኤል ይገለጥ ዘንድ... ስለዚህ በውኃ እያጠመቅሁ፡ እኔ መጣሁ።**
>
> **... ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መሰከረ። መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ ላይም ኖረ።**
>
> የመጨረሻውን ቁጥር፡ ቁጥር 32ን፡ ደግሜ ማንበብ እፈልጋለሁ።
>
> **ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መሰከረ። መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ ላይም ኖረ።**

20 ጌታ በቃሉ ላይ በረከትን ይጨምር። ከተቻላችሁ—እያንዳንዷ ቃል እንድትይዙ እፈልጋለሁ። ከኋላ ያላችሁ በደንብ ትሰሙኛላችሁ? በጣም ጥሩ፡ እዚያ ጋር ያላችሁስ ይሰማል? እየተሰማችሁ ከሆነ፤ እጃችሁን ከፍ አድርጉልኝ። በጣም ጥሩ።

21 አሁን፡ ዛሬ በዚህ ማለዳ—በምሳሌ ልንገራችሁ። በጥቂቱ ቢሆንም ምናልባት—የቤተክርስትያን ያልሆነ ሰው እንኳን ቢኖር መረዳት እንዲቻላቸው። እኛ፡ ወደቤተክርስትያን የምንመጣው እራሳችንን ለማሻሻል ነው። አመጣጣችን እራሳችንን የተሻሉ ሰዎች፣ የተሻሉ ክርስትያኖች፣ የተሻለ ዜጋ፣ የተሻለ አባት፣ የተሻለች እናት፣ የተሻለ ጎረቤት ለመሆን ነው። እዚህ መጥተን፤ በስሙ አንዳች ነገር እንድንጠይቅ ክርስቶስ ስለነገረን፡ ሁለት ወይም ሶስት ሆነን በተሰበሰብንበት ሰፍራ፤ አብሮን እንደሚሆን እና መሻታችንን እንደሚሰጠን ስለነገረን ነው። ስለዚህ፤ ዛሬ ለእኛ መልካም የሚባል፤ ከዚህ የተሻለ ምን ይሆናል እራሳችንን ለማሻሻል፣ መረዳታችንን ለማስፋት፤ ወደ ቤተክርስትያን መምጣታችንን እንደማወቅ ምን አለ? ስንቶች ናችሁ፡ “የመጣሁት ለዚህ ነው” የምትሉ፤ እስቲ እንያችሁ። “የተሻለ—መረዳት እፈልጋለሁ” የምትሉ? እንዲህ ካልሆነ በስተቀር... የተሻለ መረዳ—ሊኖረን አይችልም እናም ስለ እግዚአብሔር ማስተዋል ከፈለግን፡ ከእግዚአብሔር ቃል መውጣት አለበት፣ የተራበውን ነፍሳችንን ለመመገብ እግዚአብሔር የሰጠን ቃል ነውና። መንፈስ ቅዱስ የተላከው ደግሞ ከእግዚአብሔር ቃል ወሰዶ እኛን በቃሉ ለመመገብ ነው። ገብቷቿል? እያችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ... ቃል ከእግዚአብሔር ወስዶ እንደየፍላጎታችን እንዲሰጠን፤ ከእግዚአብሔር ተላከ።

አሁን ፣ እግዚአብሔር እኛን ለመመገብ እንዲህ ዓይነቱን አቅርቦት በማድረጉ እኔ በጣም ደስተኛ ነኝ። እናንተስ?

22 እኛ የግጦሹ በጎች ነን። እስኪ በዚህ ጉዳይ ላይ፤ ስለ በግ ትንሽ እናወራለን። እኛ የእግዚአብሄር ሶስት መአዝናዊ ፍጥረት ነን፡ እሱ እኛን ሙሉ ለሙሉ ሲቆጣጠረን ይመራናል አቅጣጫም ይሰጠናል።

23 አሁን፡ ኢየሱስን ወደ ምድር በላከው ጊዜ፡ ለእግዚአብሔር እጅግ ደስታ ነበር፤ እሱን እንደ እንስሳ ሲወከልለት ደስ ይለዋል፤ እንስሳውም ጠቦቱ ነው። ያኔ ድሮ በመጀመርያ፡ የኢየሱስ የመምጣቱ ጥላ፡ በኤደን ገነት፡ እግዚአብሄር፡ የክርስቶስን መምጣት የሚወክል ጠቦት በመውሰድ፡ በእሱ ምትክ እንደ ጥላ ሰውቷል። አሁን፤ እግዚአብሔር ክርስቶስን እንደ እንስሳ ምሳሌ፡ እንደ ህያው ፍጥረት ጥላ መጠቀሙ ሁሌ ይገርመኛል። እኛ ግን ጠቦት የመረጠበትን ምክንያት ስንመረምር፡ ስለ ጠቦት የደረስንበት፡ ጠቦት በምድር ላይ ካሉ ፍጥረታት ሁሉ እጅግ በጣም የዋህ እና ጨዋ ነው። ከበግ ጠቦት የበለጠ የዋህ እና ጨዋ የሆነ ነገር የለም፣ በራሱ-የማይኖር፡ በጣም ንፁህ ነው። ገር፣ የዋህ ትንሽ ፍጡር ነው። እብሪተኛ—አይደለም። እናም እግዚአብሔር በምድር ለመወከል ክርስቶስን ሲልከው፡ በበግ ጠቦት መሰሎታል።

24 አሁን ግን፡ እግዚአብሔር፣ ያሕዌ፣ እግዚአብሄር አባት፣ በሰማይ ለራሱ ውክልና ሲያደርግ፡ በሰማያት ከሚበሩ እእዋፋት ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሁት፣ ገር በሆነው እርግብ እራሱን ወክሏል። ከእርግብ በላይ ጨዋ ወፍ የለም። በወፎች ሕይወት እና በዱር አራዊት ላይ በጣም ጥናት አድርጌአለሁ፣ እና ርግብ በሰማይ ከሚበርር ከማንኛውም ወፍ በጣም እንግዳ ወፍ ናት። ርግብ ሀ—ሀ—አፍቃሪ ናት። ርግብ የዋህ ናት። እና ደግሞ ሐሞት የላትም፡ በወፍ ዝርያዎች መካከል ሐሞት የሌላት ብቸኛ ወፍ እርግብ ናት። ስብል እና ዘር ከሚገኝበት ሰፍራ በስተቀር እርግብን በየትኛውም ቦታ የማታዩበት ምክንያት ይህ ነው። አሁን፡ በ...

25 በታቦቱ ውስጥ፡ ርግብ ነበረች። ርግብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታዎች ተወክሏል። መንፈስ ቅዱስን ትወክላለች። ደግሞም በግ በራዕይ ውስጥ፤ እንደ ክርስቶስ፤ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ቦታዎች ውስጥ ተወክሏል፣ ወደ ኋላ ከዘፍጥረት ጀምሮ፤ እርግብም ቢሆን ያው ነው።

26 በዘፍጥረት መጽሐፍም፤ ርግብ በመርከብ ውስጥ ነበረች፣ ከሌሎች በአየር ላይ ከሚበሩ እእዋፋት ጋር፡ አንዱ ቁራ ነው፣ ከነ እሞራ ጋር—በጎጆዋ ነበረች። እና ቁራ ማለት ሰግብግቦች ከሚባሉ እኣእዋፋት ዋናው ነው፡ እንደሚመስለኝ፡ ሰግብግብ ከሚባሉ እእዋፋት መካከል፡ ቁራ እና ጄይበርድ ናቸው። ቁራ ረጅም-ዘመን የሚኖር ወፍ ነው፡ ብዙ ይቆያል (እንደሚባለው) ቁራ... አንዳንድ ጊዜ፡ ወደ፡ ሁለት ወይም ሶስት መቶ ዓመታት፣ በቀቀን ደግሞ ከዚያ በላይ ይኖራሉ።

27 ርግብ ግን ሀሞት እንኳን የሌላት እንስሳ ወይም ወፍ ናት። አሁን ቁራ፡ እዚህ ቁጭ ብሎ ከሞተ ሬሳ ሊበላ ይችላል። ርግብ ግን በሞተ እካል ዙርያ ፈጽማችሁ አታዩአትም። ያንን መቋቋም አትችልም። እፍንጫዋ ያንን ግማት መቋቋም አይችልም። ያጥወለውላታል። የበሰበሰ እና፣ የተበላሸ ነገር ፊት እንዲሁ መቆም አይችሉም። አይቋቋሙትም፡ ስለዚህ አትበላም። ብትበላ

ግን እርግቢቱን ወድያው ይገድላታል፣ ምክንያቱ ምግብን የሚፈጨው ወደ ጨጓራ ውስጥ የሚፈስው ሀሞት ነው ምግቡን የሚያደቅቀው። እናም ይህንን ሂደት ሊሰራ የሚገባ ሀሞት ከሌለ፡ እርግቢቱን ይገድላታል። ስለዚህ ሁልጊዜ እርግብ ንጹህ ነገር በሚገኝበት ስፍራ ላይ፤ ጤነኛ በሆነ ስፍራ ትገኛለች።

28 ቁራ ግን፡ ይለያል። አሁን፡ ቁራ ማለት የግብዞች ምሳሌ መሆኑን አስተውሉ። ቁራ እዚያ ጋር—በወደቀ ሬሳ ላይ ቁጭ ብሎ እስኪበቃው ድረስ መብላት ይችላል፤ ከዛ በኋላ ደግሞ በርሮ ወደ ማሳ በመሄድ፡ ስንዴ ይበላል። ርግብ ግን ስንዴን ተመግባ ከወደቀ ሬሳ ለመብላት አትበርም።

29 ስለዚህ፡ ግብዝ ሰው፤ መንፈሳዊ ነገሮችን እየተመገበ፣ መልካሙን እና ክፉውን እየበላ ግብዝ ሊሆን ይችላል። ዳግም-የተወለደ ትክክለኛ ክርስትያን ግን ስሕተትን አይቋቋምም፡ ንጹሕ ነገር ብቻ ይበላል። ይሄን አስተውሉ! ለመደነስ እና ለመጠጣት ፤ ወደ ጭፈራ ቤት እየሄደ፤ በሐጢአት የሚኖር ወዳጅ ስታዩ፤ ደግሞም ወደ ቸርች መጥቶ ልክ እንደ ጻድቅ ሲጮኽ፤ ይህ ምንድርነው? የበሰበሰውን እና መልካሙን መብላት የሚችል፡ ጥምብ አንሳ ነው። እውነተኛው ክርስትያን ግን ከሞት ወደ ሕይወት ስለተሻገረ፡ እነዚህን ነገሮች መቋቋም አይችልም። ማሰቡ እንኳን ሳይቀር፤ ወድያው ይኮንነዋል፤ ፊቱን አዙሮ እስኪሄድ ድረስ እስኪፈርድበት ድረስ ይኮነናል። ኦህ ፣ እንዴት ያለ ሰዕል ነው!

30 አሁን፤ የበግ ጠቦት ደግሞ፤ እራሱን እንኳን መርዳት የማይችል፡ እጅግ ጨዋ ፍጥረት ነው። በራሱ-የማይደገፍ ነው፡ ምክንያቱንም እራሱን መርዳት አይችልም። ከጥቂት ዓመታት በፊት ተሽከርካሪ ጥበቃ እየሰራው በግጦሽ በኩል ሳልፍ፤ የበግ ጠቦት አገኘው፡ በተጠቀለለ አደገኛ አጥር ሰር ቆሳስሎ ስለነበረ፡ ብዙዎቹ እንዲሁ ራቅ ራቅ አሉበት። ይህ ሚስኪን ፍጥረት፡ እየደማ እና እየጮኸ እዚያው ተጋድሟል። እናም ግማሽ ማይል ርቀት ያህል ዞር ብየ፡ ወደ ማዶ፤ ሙሉ የበግ መንጋ አየሁ። አሁን፡ እዚያ ቢቆይ ኖሮ ወዲያውኑ ቁራዎች መጥተው ከዓይኖቹ ባነሱ ነበር። ባናድነው ነሮ። ነገር ግን ሚስኪኑን ፍጥረት አነሳሁት እና፤ ቁስሎቹን ጠራርጌ አቀፍኩት። ወደ እቅፌ አነሳሁት። ዝም ብሎ ታቀፈ። ፈጽሞ እምቢ አላለም። ምናልባት’ኮ፤ የሰው እጅ የነካው መጀምርያ—መጀመርያ ቀኑ ይሆናል፤ እሱ ግን ጨዋ ነው። ለመመራት ፈቃደኛ ሆነ። ለእርዳታ ፈቀደኛ ነበረ። እንዳያችሁት ተሰፋ አደርጋለሁ። ላለመቃወም ወይም ላለ መማታት እና ላለ መናከስ፤ ፈቃደኛ ነበር። የበግ ጠቦቶች አይማቱ፣ አይናከሱም፣ እራሳቸውን ዝቅ የሚያደርጉ ናቸው። እና ይህ ታናሽ ፍጥረትን፤ አነሳሁታና ከሌሎች በጎች ጋር እንዲቀላቀል አደረግኩት። ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ እናቱ ስታገኘው፤ እንዴት ደስ እንዳለው! አሁን፤ ይሄ የእግዚአብሔርን በግ እጅግ ይገልጻል!

31 ታውቃላችሁ፤ በግን ወደ መታረድ ሲነዳ፡ በግን ወደ እርድ ስፍራ የሚመራው ታውቁታላችሁ፡ ፍየል ነው። ፍየሉ በጉን በቀጥታ ወደ እርድ ቤት እንዲገባ ይመራዋል፡ ከዛ በኋላ፡ በጉ ወደ ማረጃው ረድፍ የሚገባበት ሰዓት ሲደርስ፡ ዘልሎ ይፈረጥጣል። ነገር ግን፡ ኦህ፡ ፍየል ሲታረድ ግን፡ ይላሉ፤ ወድያውኑ አቧራ ያስነሳል። አያችሁ?

32 ስለዚህ ዲያብሎስ የሚያደርገውም ይሄው ነው። የእግዚ አብሄርን ልጆች በጣም እስከፊ ወደ ሆነው ነገር ለመምራት ይሞክራል፡ ለመሞት የራሱ ጊዜ

ሲደርስ ግን፤ አቧራ እስኪያነሳ በጣም ይወራጫል። ዲያብሎስ የሚሰራው እንዲህ ነው። አንዳንዴ፡ ቅምጥል-ልጃገረዶች ላይ እና ጨብራራ ወንዶች ላይም እንዲሁ፡ አንዲት ልጃገረድ በፓኬት ሲጋራ ወይም በአንድ ጠርሙስ ዊስኪ፡ ገደል ትገባለች፤ የእከሌ ጠቦት፡ ከመንጋው ወደ ገደል ያስታል። "አይ፤ ምን ችግር አለው። የቤተክርስቲያን ደህና-ደህናውን ነገሮችማ ምንም ችግር የለውም።" ነገር ግን ሞት መጥቶ ይሄን ሰው የዳሰሰው እለት፡ ሲያቃስት፣ እና ሲንከባለል አገር ሲያዳርስ ትሰሙታላችሁ። ዲያብሎስም እንዲህ ነው።

33 የበግ ጠቦት ግን፡ እንዲሁ ለመነዳት ሲበዛ ጨዋ ነው። ስለዚ እግዚአብሄር ክርስቶስን እንደ በግ፤ እራሱን ደግሞ እንደ እርግብ የመሰለበት ምክንያት ይህ ነው። ዮሃንስ ኢየሱስን በዮርዳኖስ ወንዝ ባጠመቀው ቀን፡ ከተፈጸሙ ነገሮች መካከል አንዱ እና ዋናው ነገር፤ የተፈጸመው በዚያ ሰፍራ ነው። እንዴት እንደሚያምር አሰቡት! በምድር ፍጥረታት መካከል ትሁቱ፤ የበግ ጠቦት፡ እና በሰማይ ከሚበሩ እጅግ ትሁቷ፡ እርግብ። አሁን፡ ሕብረት ያደረጉበት ብቸኛው መንገድ ይሄው ነው። ርግብ በግ ላይ የወረደችበት ብቸኛው ምክንያት ይሄው ነው። አሁን፡ ርግቧ ስትወርድ፡ ዮሃንስ ኢየሱስን አይቶ፡ እንዲህ አለ፦ "እነሆ የዓለምን ሐጢያት የሚያስወግድ፡ የእግዚአብሄር በግ።" ዮሐንስም፡ "መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ ላይም ኖረ" በማለት ተናግሯል። ሀሌሉያ! ይሄው ነው። ርግብ እና በግ አንድ የሆነበት። እግዚአብሔር እና ሰው አንድ የሆኑበት። ሰማይ እና ምድር የተቃቀፈበት። ሀሌሉያ! ያኔ ነው እግዚአብሄር፡ ወርዶ ሰጋ የለበሰበት፡ እግዚአብሄር መንፈስ ከመሆን ወርዶ እንደ ሰው በመሆን በእኛ መካከል ያደረበት። ያኔ ነው ዘለአለም ሁሉ በአንድ የተቃቀፉባት። የወደቀው የሰው ዘር የአዳም ህዝብ እና ያሕዌ እግዚአብሄር ከመላእክት ሁሉ ጋር አንድ የሆኑባት፡ እግዚአብሄር እና ሰው አንድ የሆኑባት፤ ዮሃንስ ኢየሱስን ያጠመቀባት ታላቅ የመታሰቢያ ቀን ይህች ናት።

እስኪ፡ ተኩላ ቢሆኑ ኖረውስ? መልካሙን የእርግቧ ዝማሬ በተኩላ ፊት ባልተሰማ ነበር።

34 አመሻሽ ላይ ጥንታዊቷ እርግብ ባለችበት ሆና ስትዘምር እንደመሰማት ምን ደስ የሚያሰኝ ነገር አለ? ሚስቴን እና ልጄን ካጣሁ በኋላ... የማደርገውን ለማንም እላሳውቅም ነበር። ባረጀች መኪናየ ውስጥ እገባና፡ በዚህ በኩል ባለው ጎዳና እየነዳው፡ ዋልነት ሪጅ መቃብር ሰፍራ እሄዳለሁ፤ ከዛፍ ስር ቁጭ ብየ መቃብሩን እመለከታለሁ። በቃ ልቋቋመው የምችል አይነት አይመስልም። በነሱ ላይ ተሰፋ መቁረጥ ተሳነኝ። ህጻኗ ልጄ፡ በሰምንት ወሯ፡ እዚህ ተኝታ፡ አስባታለሁ። ወደ እኔ ለመምጣት ትንንሽ እጆቿን እንዴት እንደምትዘረጋቸው፡ እኔም ክላክስ ሳደርግላት ወይም የሆነ ነገር ሰናገራት፡ እጆቿን ዘርግታ፤ "ጉ-ጉ፡" ትለኛለች። እና በተለይም ምሽት በሚሆንበት ጊዜ፡ ከዛፍ አጠገብ እቀመጥ ነበር። እናም ዝማሬዋን የምታደርግ፤ ጫካው ውስጥ የምትቀመጥ የተለመደች እርግብ ነበረች። ኦህ፡ ማይ! እንዴማ እኔን ለማናገር ተመልሳ የምትመጣ የማትሞት የልጄ ነፍስ ነች ወይ ብየ አሰብኩ። እንደ ርግብ ዝማሬ የሚጣፍጥ የለም። መልካም ወሬ የምታመጣ። ሰላም ለመፍጠር ጥረቷ! ፍቅር ነገር ናት! ጠዋት በማለዳ፤ በመኖርያየ አቅራቢያ ወዳለው ደን ሄጄ፡ ሰሰማው እንዴት ያለ ሰላማዊ ነው! በረዣዥሞቹ ዛፎች ላይ ተቀምጠው፡ ርግቦቹ አንዱ ለሌላው ይዘምራሉ።

35 በቀደምለት፡ እነ ወንድም ኮክስ ጋር፡ ሁለት ልጆች የነበሯት አንዲት ርግብ ነበረች። እና ድመቶች እንዳይበሏቸው፡ ጣራው ላይ ተቀምጠዋል። አሮጌትዋ እናት ርግብም ትመግባቸዋለች። ከዛ በኋላ መጥታ ወደ ዛፍ እንዲወጡ ትረዳቸዋለች፤ አንደኛው በሌላው ላይ አንገቶቻቸውን ይሰቅሉና፤ ሁለቱ ታናናሽና፤ ጨዋ ርግቦች፤ ቀኑን ሙሉ በፍቅር አብረው ይዘምራሉ።

36 እናም እግዚአብሔር እንዴት እንደሆነ አሰብኩት (ርግብ እንደዚህ አፍቃሪ ወፍ ናት) እና ርግቡ እግዚአብሔር፡ ከሰው ልጆች ጋር፡ ፍቅርን ማድረግ ይፈልጋል። እግዚአብሔር መፈቀር ይወዳል። ጌታ ሊያፈቅራችሁ ይፈልጋል። "እግዚአብሔር ዓለሙን እንዲሁ ስለወደደ፤ አንዲያ ልጁን ሰጠ፡ በእሱ የሚያምን ሁሉ የዘለአለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ፡ እንዳይጠፋ።" ጌታ የተባረከ ይሁን! ስለዚህ እግዚአብሔር፡ ፍቅርን ለማድረግ በመፈለጉ፡ የሚያሰወድደው ነገር መሰራት... ነበረበት። እንደሱ ዓይነት ጨዋ ነገር መሰራት ነበረበት። ከራሱ ተፈጥሮ አንዳች ነገር ማድረግ ነበረበት። ሊፈቀር የሚችል ነገር ማዘጋጀት ነበረበት።

37 ከእናንተ ተፈጥሮ ውጪ ልታፈቅሩ አይቻላችሁምና። አፍቃሪ ከፍቅር ጋር አንድ መሆን ይኖርበታል። ልኩን ካሰጠበቁት፡ ባልና ሚስት መፋቀር አለባቸው። ልካቸውን የሚጠብቁ ከሆኑ፡ ቤተሰብ መፋቀር አለበት። ሊፈቀር የሚችል ነገር! የምታፈቅሯት ሚስት እንድትሆንላችሁ፡ ሴት ፍለጋ የትም ትወጣላችሁ። እሷም የምታፈቅረውን ባል ፍለጋ፡ ትወጣለች።

38 እግዚአብሔርም፡ የሚያፈቅረ ነፍስ ለማግኘት ይጥራል። ስለዚህም፡ እራሱን በምድር ላይ እንደ ጨዋ ርግብ እና ጨዋ የበግ ጠቦት መሰሏል። በጉ ለደቂቃም ያህል አኍረጥራጭ የተኩላ ዓይነት ባህርይ ቢያሳይ፡ ርግቧ መብረሯን ወድያውኑ ባደረገች ነበር፡ በራቀች ነበረች።

39 የበግ ጠቦት-ግን-ታላቅ-የሚለው የራሱ ሐሳብ የሌለው ነው። የበግ ጠቦት ሲጠፋ፡ አንድ ነገር፡ ተሰፋ እልባ ሆኖ ይጠፋል። በግ መመለሻው አያውቅም። ፍየል ወደ ሞት የሚመራበት ምክንያት ይሄው ነው። በግ ሲጠፋ፡ መመለሻውን አያውቅም። እግዚአብሔር እኛን በበግ የመሰለበት ምክንያት ይህ ነው። ከጠፋን፡ ጠፋን ነን። እርሳችን የምናውቅበት ምንም መንገድ አይኖርም። አንድ መንገድ ብቻ አለችን፡ እሷም እርሳችንን ለመንጋው እረኛ አሳልፎ መስጠት፡ ከዛ በኋላ እሱ መሪ ይሆነናል።

40 አሁን፡ ይሄን ሳስታውቃችሁ ጠቦቱ እና በጉ አንድላይ... ማለት፡ ጠቦቱ እና ርግቧ፤ ሁለቱ፡ አንድ ይሆናሉ። ከዛ በኋላ እርግቧ ጠቦቱን፡ የእግዚአብሄርን ልጅ እንዴት እንደምትመራ ተመልከቱ፡ ወደ መታረድ መሆኑን እያወቀ፡ እንዴት ያለ ጨዋ እንደነበረ ተመልከቱት። ምን አይነት ጨዋ ነበር፤ እራሱን ዘወትር፡ እራሱን-የቻለ እርጎ እንዳይቆጥር ይጥራል። "አስቀድሜ ከአባት ካላየሁ በቀር ከራሴ አንዳች አላደርግ፤ አብም በእኔ ይኖራል።" አለ።

41 ሌላው፡ የበግ ጠቦት ሌላ ነገር፤ በግ መብቶቹን ለመስጠን ፈቃደኛ ነው። እግዚአብሔርም፡ በጎች እንድንሆንለት ይፈልጋል፤ ብዙውን ጊዜ ግን መብቶቻችንን አስልፈን መስጠት፣ መብታችንን መተው አንወድም። ብዙዎቻችሁ፡ "ወንድም ብራንሃም፤ መብቴ'ኮ ነው።" ትላላችሁ። ትክክል ናችሁ፤ ነገር ግን መብታችሁን ለመስጠት ፈቃደኞች ናችሁ? እግዚ አብሄር

ይመራችሁ ዘንድ፤ መብቶቻችሁን ለመስጠት ትፈቅዳላችሁ? ዛሬ ዛሬ፤ ያለው ችግር በአብያተ ክርስትያኖቻችን፣ በብዙዎች ዘንድ፣ የእግዚአብሔር በግ ጨዋነት የለም... በጎች መሆን ይኖርብናል፤ ሌላው ሁሉ ሆነናል በጎች ከመሆን በቀር። እንዲህ አይነት ባህርያት ማምጣት ስንጀምር፡ የመንፈስ ቅዱስ ርግብ በርራ የምትለየን፤ ምክንያቱ ይሄ ነው።

42 የእግዚአብሔር በግ ያኔ በመጀመርያ እንደ ተኩላ ቢያጉረጠርጥ ኖሮ፤ ወይም ጨዋዋ ርግብ እንዲያደርግ ከፈቀደችለት ውጪ ተቃራኒ ቢያደርግ፤ እርግቢቱ በርራ በሄደች ነበር። በደቂቃ ውስጥ ትሄድ ነበር።

43 ዛሬ፤ “የጴጤቆስጤ ምዕመናን ምን ነካቸው?” እያሰባለን ያለው ምክንያቱ ይኸው ነው። የተለየ ሌላ ተፈጥሮ ስለተላበስን ነው። “ትክክል የመሰለን ነገር እናደርጋለን። መብታችንን እንፈልጋለን።” የሚል ጠፈጥሮ ተላብሰናል። እናም ትዕቢተኞች ሆነናል። ጠላቶች ሆነናል። ግዴለሽ ሆነናል። ቁጣን አስገብተናል። ራሰወዳድ እንድንሆን ፈቅደናል።

44 በግ ግን፡ መቼም ጸጉሩ እንኳን የራሱ ነው፡ መብቱ ነው። የጸጉሩ ባለቤት እሱ ነው... ጊዜው ሲደርስ ግን፡ በጉን ወሰደው ወደ ጥግ ጎትተው፤ እጅ እግሩን ያስሩታል። በጭራሽ አይማታም፤ በፍጹም አይራገጥም። በግ ስለሆነ፤ መብቱን ከላዩ ላይ ወድያው መግፈፍ ትችላላችሁ። ይህ ተፈጥሮው ስለሆነ፤ ሌላ ሊያደርገው የሚቻለው ነገር የለውም። ግን እስኪ የአንድ ክርስትያን መሰመር አንዲት ጊዜ እለፏት፤ በግ ይሁን ፍየል ያኔ ትለዩታላችሁ። ብቻ መሰመሩን አንዴ እለፍ፤ ማን እንደሆነ ታውቀዋለህ። አብያተ ክርስትያኖች አሁን ያሉበት ሁኔታ ውስጥ ያስገባቸው ነገር ምክንያቱ ይህ ነው።

45 እራሳችንን የእግዚ አብሔር ብግ ብለን መጠራራት ጀምረናል። ወንዱም ሴቱ፤ ሁሉ፤ እንደ እግዚአብሔር በግ ከመሆን በቀር፤ ሁሉን ማድረግ ጀምረዋል። ጸጉራቸው ተቆርጦ፣ ጸጉሮቻቸው ጥቅልል ሰቅለውበት፣ በአጭር ቀሚስ፤ ጎዳናው ላይ ሲንሸራሸሩ ታያላችሁ። ከጥቂት ዓመታት በፊት፤ ምን ይባል ነበር... እነሱን... እንዲህ የሚያደርጉትን አትቀጥሩም ነበር። አሁን ግን ቤተክርስትያን እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ መዘፈቋ ያስገርማል። ትሑቱ ጨዋነታችሁን ከመጠበቅ ይልቅ፤ የፍየል እና የተኩላ ባህርይ ስለወረሳችሁ ነው። ደግሞ፡ “መብቴ ነው፡ ወንድም ብራንሀም” ትላላችሁ። መብታችሁ እንደሆነ አውቃለሁ። “ጸጉር አስተካካዮች ጸጉር ይቆርጣሉ። የጸጉር ባለሞያዎች ጸጉር እስከቆረጡ ድረስ፤ እኔስ መብት የለኝም?” አዎን ልክ ነው፤ የአሜሪካዊነታችሁ መብት ነው። በግ ለመሆን ግን፤ ይህን ሁሉ ለመናቅ ፈቃደኛ ናችሁ? እራሳችሁን ለማስገዛት ትፈቅዳላችሁ?

46 እናንት ሴቶች፤ ሩቅኮ አይደለም፤ ጎዳና ስትወጡ... ሴቶች ዛሬ ዛሬ የሚለብሱትን ልብስ ለማየት ያሳፍራል። ስለ ፕረስቢተርያኖች እና ስለ ሜተዲስቶች አላልኩም፤ የማወራው ስለ ሆሊነስ ሴቶች ነው። በየጎዳናው ስላሉ፡ እንደው...

47 በመኪናየ ፊት ለፊት የተንጠለጠለ መስቀል ነበረኝና፤ አንድ ሰው እንዲ አለኝ፦ “ቢሊ፡ ይህ የካቶሊክ አርማ መሆኑን ታውቃለህ?” አለኝ።

48 በፍጹም! “መቼ ነው ካቶሊኮች መስቀሉን ምርጫቸው የሆነው?” አልኩት። የክርስትና እምነት ሰንደቅ ዓላማ ነው እንጂ፡ የካቶሊክ እምነት አርማ

አይደለም። የካቶሊኮች እምነት ጻድቅ በሚባሉ ሙታን ላይ ነው፤ በማርያም ላይ ወይም—ሌሎች በሚያመልኳቸው ሙታኖች። እኛ ግን ሙታንን አናመልክም። ቅዱስ ሴሲልያም ይሁን ሌሎች ቅዱሳንን አናመልክም። ይህ ለእነሱ፡ መንፈሳዊ ከፍታ የሚሉት ካቶሊካዊነት ነው። መስቀሉ ግን የሞተውን ከሙታንም ዳግም የተነሳውን የሚወክል ነው።

49 ስለዚህ እንዲህ አልኩ፦ “ጎዳናዎቹን እያየሁ፡ እጠብቃታለሁ። የዛሬ ሀያ-አምስት ዓመታት በፊት፡ ወይም ሰላሳ፡ ዓይኖቼ ለመታወር በደረስ ጊዜ፤ ዓይኖቼን ብትፈውሰልኝ ቅን ነገርን እከተላለሁ ብዬ ለእግዚአብሔር ቃል ገባሁ።” እናም እንዲህ አልኩ፡ “የሚታየው ሁሉ፤ እጅግ አምላካዊ አይደለም፤ ሴቶች በየ ጊቢው እና በየቦታው እራቁታቸው፣ አጫጭር ቀሚስ የለበሱ ሴቶች። ስለዚህ የዲያብሎስ ነገሮች ከማየት፡(ክርስቶስ ለእኔ ያደረገልኝ ትዝ አለኝ እና፡ ፊቴን መለስኩ) መስቀሉን ተመለከትኩ።” ሃሌሉያ!

50 ስለዚህ እናንተ ሰዎች… ይህ “የፕረስቢተርያን ነው፣ ካቶሊክ ነው፣” አትበሉ፡ የጴንጤቆስጤ ነው! አሜን። “ወንድም ብራንሃም፤ መብት አለኝ።” ብትሉኝ፤ አዎን ልክ ናችሁ፤ ይሁን እንጂ በግ ብትሆኑ፤ መብቶቻችሁን ትንቁ ነበር። ስለዚህ እንዲህ አይነቱ ድርጊቶች ውስጥ ስትገቡ፤ መንፈስ ቅዱስ፣ ማለት ጨዋዋ ርግብ፡ ውድያውኑ በራ ትሸሻለች። ከእናንተ ጋር መዋረድ አትፈልግም። አይ፡ አይ፡ አይ። እንዲህ ዓይነት ተግባር እየፈጸምክ መንፈስ ቅዱስ አብሮኝ ይቆያል ብለህ አታስብ። አይሳካልህም! መጽሐፍ ቅዱስ ተናግሯል። ነገሮችህን ማራገፍ አለብህ… እንዴ፡ “ሌሎች ሴቶች ያደርጉት የለም’ዴ” ትያለሽ።

51 እናንተም ወንዶች፡ እናንተ ምስኪን፣ ጨቅሎች፣ አጥንት አልባ፣ ሴታሴቶች፡ እናንተ፡ ሚስቶቻችሁ እንዲህ ያሉ ነገሮች እንዲያደርጉ የምትፈቅዱ፤ ይህ የተሰራችሁበት ያስረዳል። አለኝ እንደምትሉት ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ያላገኛችሁበት ምክንያት ይህ ነው፤ ወይም ደግሞ፤ አብራህ እስካለች ድረስ እንደ ክብርት ሴት እካሄድ ለማስኬድ በቂ ነገር ሊኖርህ ይገባል፤ አሜን። የድሮ-ዓይነት አቆራረጥ እንዲህ ይመስላል። ግን ደግሞ ቤተክርስትያን የሚያስፈልጋት፤ የድሮ-ዓይነት፡ መንፈስ ቅዱሳዊ የሆነ እጥበት፣ ማስጣት እና መድረቅ፣ በመንፈስ ቅዱስ መተኮስ፡ ያስፈልጋታል። በትክክል!

52 ዓለም የገባችበት ዓዘቅት! በየጎዳናው ወጥተው የሚያሳዩት ተግባር! እናንተም እሮብ ማታ ፊታችሁን ቴሌቪዥን ላይ ሰክታችሁ፤ ቤተክርስትያን አትሄዱም! እንደው እናንተስ… ለምን፡ በመላ አገሪቱ… የዴቪድ ክሮኬት ማንነት የማያውቅ አንድ ህጻን የለም። በሶስት ዓመቱ ድብ እንደገደለ የሚናገረው፤ ቆሻሻ ውሸት፤ ውሸት መሆኑ ታውቃላችሁ፤ የልጆቻችሁ ራስ ግን በዚያ እንዲሞላ ትፈቅዳላችሁ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከመቶ አንድ ፐርሰንት እንኳን ያህል ትንሽ ነገር የሚያውቅ የለም። ይህ ዓለም እጅግ ሰልተበላሸ ነው! ይህች፤ ከእግዚአብሔር እጅግ የራቀች አሳፋሪ አገር፤ መንፈስ ቅዱስን ተቃውማለች።

53 እንደው፡ “እኔ’ኮ ቤተክርስትያን ሄጄ እጮኻለሁ፡” ትላላችሁ። ይሄን ታደርጉ ይሆናል። ነገር ግን፡ ጨዋው የእግዚአብሔር በግ በልባችሁ አርፎ፡ ህይወታችሁን እንድታነጹ እና እንደ ሌላ ሰው እስኪያደርጋችሁ ድረስ፡ ክርስትናን ማስመሰላችሁ አይጠቅማችሁም። ልትጨብጡት ያስፈልጋችኋል። አሜን።

54 በቅርቡ የታመምን ሰው ለመጠየቅ፤ ወደ አንድ ቤት ሄድኩ፤ እና አንዲት እመቤትም እዚያ ጋር ቅጭ ብላ፡ አርፋለች። እና አንድ ኮፍያውን ከጭንቅላቱ ወደ ጎን ዘመም ያደረገ፤ አፍላ መጣና፤ “ማሚ፡ እራት ደርሷል? ” አለ።

55 እንዲህ አለችው፤ “ዛሬ ማለዳ እራት ለማዘጋጀት፡”፣ “ዛሬ ጊዜ አልነበረንም፡ ማርየ፤” አለችው። “ሳንድዊች እየሰራሁልህ ነው” አለች፣ “ብርቱካንም አለ።” አለችው።

56 ጠጋ ብሎ ብርቱኳን አንስቶ፡ በደንብ አየውና፡ ነከሰው፡ ከዛ በኋላ ባለውና በሌለው ሃይሉ ወርውሮ ግድግዳው ጋር አጋጨው፡ ጭማቂውም ወደ ታች ፈሰሰ፤ እንደ ቀላል ነገር፡ “እዚህ ቤት ያለሽ ይህ ብቻ ከሆነ፡ እወጣለሁ፡” አለ።

57 “ጌታ ሆይ፡ ለአምስት ደቂቃ ያህል እንኳን የኔ በሆነ!” ብየ አሰብኩ። አባቱ፡ ተገፎለት እንደማያውቅ አድርጌ ቀልቡን እገፍለት ነበር! ግን እነሱ አዝነውለት እና ወድደውት፡ ቁጭ ብለዋል። የሚያስፈልገው ግን የድሮው-ዓይነት አቀጣጥ ነው። እኛ ሁላችንም የሚያስፈልጉን፤ የድሮ-ዓይነቶቹ ቤቶች ናቸው። ከመሰውያው በስተጀርባ ቆመው እውነትን የሚሰብኩ ሰባኪዎች፣ መድረስ ወዳለበት ሰፍራ የሚያደርሱ። አሜን። ይህ እውነት ነው። ኦ፡ ማይ!

58 ህጻን ሜሪ፤ ይላደጉትን እግሮቿ ጣል አድርጋ፣ ትንሿ አፍንጫዋን ወደ ላይ ቀልበሰ ገና ያላደገን ከንፈሯ (በማክስ ፋክተር አሸንክታብ) በሮዝ-ቀለም አየር ላይ አሽብርቃ፡ ራሷን ቀና በማድረግ ከቤት ትወጣለች። ምን ዓይነት ዉርዴት ነው! ምን አይነት የማይታዘዙ ልጆች ተፈጠሩ! መጽሀፍ ቅዱስ እንደሚመጡ ተናግሯል። ቅዱስ ቃል እንዲህ ይሆናሉ ብሏል። እንዴት እንደሚሰሩ፣ እንዴት እንደሚያደርጉ፣ እና ዛሬ በዓለም እየሆኑ ያሉትን ነገሮች ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስን በማሳዘናቸው ምክንያት ነው።

59 ጥቂት ዓመታት በፊት ነው። በቅርብ ቀናት፣ መንፈስ ቅዱስ ለመጀመርያ ጊዜ በአሜሪካ ላይ የወረደበትን ቀን ለማሰብ እሄዳለሁ፡ የዛሬ ሐምሳ ዓመት፡ በድሮዋ የአዙዛ ጎዳና በነበረው ኮንፈረንስ፡ በሎስ አንጀልስ ጴንጤቆስታል ኮንፈረንስ፣ ህዝብ በተሰበሰበ ጊዜ፡ መንፈስ ለመጀመርያ ጊዜ የወረደበት ሰፍራ ነው። ክርስቶስ በነዚያ ሰዎች ላይ ሲወርድ፡ ሰላማውያን፤ ጨዋ ሰዎች ነበሩ። አምላካዊ ኑሮ ይኖሩ ነበር። የመሰዋዕት ኑሮ የሚኖሩ። እራሳቸውን ለመሰጠት ፈቃደኞች የሆኑ። በመንፈስ ቅዱስ ለመመራት የሚፈቅዱ ነበሩ። ህዝብ ስለሚለው ነገር ግድ አይሰጣቸውም፡ “ጥንታዊ-ቅኝት፡” የተቃኙ ናቸውና። “ዕብዶች” ናችሁ ቢባሉ ወይም ሌላ ቢሉ፡ በመንፈስ ቅዱስ ለመመራት ፈቃደኛ ነበሩ።

60 ዛሬ፡ ግን፡ ኦ፡ ማይ፤ አንዲት ብናኝ ዱቄት እና የሜክ-አፕ ሳጥን ጋር፣ በቁምጣ ሱሪ፡ ጎዳና ላይ ይወጣልኛል፡ “ከመንፈስ ቅዱስ ጋር” እራሳቸውን ይጠራሉ። ለምን፡ ውርዴት'ኮ ነው! ኦህ፡ “ግን'ኮ በልሳን እናገራለሁ፡” ትላላችሁ። አዎ፡ ዲያብሎሰም፡ ይናገራል። “ኦህ፡ እኔ'ኮ እጮኻለሁ።” ዲያብሎሰም፡ ይጮኻል። ዲያብሎስ፡ ከፍቅር ውጪ፤ የእግዚ አብሔር የሆነውን ሁሉ ማስመሰል ይችላል፤ ፍቅርን ግን ማስመሰል አይችልም። አዎና።

61 ከዚያ፡ እነዚህን ነገሮች መፈጸም ስትጀምር፡ መጀመርያ የሚሆነው ታውቃለህ፡ እጥሮቹን ታፈራርሳለህ፡ ማመቻመች ትጀምራለህ፣ ከዚያ ቤተክርስቲያን መለቃቀም ትጀምራለች፣ ሌሎች እንዳይመጡ ከልካዮች

ይገቡባታል፣ ይሄኛው፡ “ታውቃለህ ፓስተሩ፡ በቃ’ኮ እከሌ-እና-እከሌ፡” ወይም “ዲያቆናቱ እከሌ-እና-እከሌ፡” ይላል። እና፡ እናንተም የመጀመሪያው ነገር፡ ያንን ታዳምጡታላችሁ! እናም ብዙ ችግሮች የሚያጋጥሙን ምክንያቱ ይህ ነው፡ ዲያቢሎስን መስማት ስለጀመራችሁ፤ የዋሁ ርግቡን ከማዳመጥ ይልቅ አጉረጥራጩን ታገኛላችሁ። ከሚመራችሁና መንገድ ከሚያሳያችሁ፣ ከሚያፈቅራችሁና ከሚባርካችሁ የእግዚአብሔር ርግብ፡ ይልቅ።

62 ቅንጣት ታክል የቁጣ ስሜቶችን ማውጣት የጀመራችሁ ለታ፤ ርግቧ ወድያው ትበራለች። ይህ እውነት ነው። ተፈጥሮዋ የተለየ ነው፡ ይሄን መታገስ አትችልም። ኦህ፡ ይሄን በፍጹም አትታገሰም። ሄደህ ጎረቤትህ ስታማ፡ አትታገሰም፡ በቃ እንዲህ ካለ ነገር ጋር አትተባበርም። ወድያው ይበራል መንገዱን ይቀጥላል። ከዚያ ወዲያ መታገስ አይችልም። ርግብ ጨዋ ነው። ርግብ ትሁት ናት፡ እናም እርግብ፡ እና—ከሷ ተፈጥሮ ጋር አንድ ከሆነ በቀር መቆየት አትችልም።

63 አሁን፡ እግዚአብሔር ሌላ ተፈጥሮ ሊያደርጋችሁ ይችላል። ሴትም ይሁን ወንድ፡ ሌላ ባህርይ ሊሰጣችሁ ይችላል። እናንተም፡ “እንግዲህ፡ ውንድም ብራንሃም፡ ምን እናድርግ? ” ብላችሁ ብትጠይቁኝ። በቃ እንደገና በግ ሁኑ። ሁለቱ እንስሶች ብቻ ይተባበራሉ፡ እነሱም ርግብ እና በግ። ርግብ ከበግ በቀር በሌላ ላይ አታርፍም። ስለዚህ ፍየል ሆናችሁ እንደሆነ፡ ያረጀውን የፍየል መንፈስ ከራሳችሁ አራግፉት። ትክክል ነው። ሌላ ነገር ሆናችሁ እንደሆነም፣ ሐሜት ከጀማመራችሁ፡ ከእናንተ አርቁት።

64 እዚህ አንድ ጊዜ አንዲት ከተማ ውስጥ፡ መሰበክ የተቻለኝን ያህል ሰበኩና፡ እና እጅግ ብዙ ህዝብ ነበረ። የመሰውያው ጸሎት ጠራሁ። የሐጥያትን አድማስ ሁሉ ጨርሼ ዳስሼዋለሁ፡ የማስበው ሁሉ አዳርሻለሁ ብየ አሰብኩ። ጉባኤው ካለቀ በኋላ የዛኑ ቀን ማታ ላይ፡ እጅግ ስሜታዊ የሆነች አንድ ሴት መጣችና፡ “መቼም፡ ወንድም ብራንሃም፡ ዛሬ እኔን ሰላልነካኸኝ እጅግ ደስ ብሎኛል፡” አለች።

“እኔን አልነካኸኝም ዛሬ፡” የምትል። “እውነተኛ ክርስትያን መሆን አለባት፡” ብየ አሰብኩ።

65 እኔም አልኳት፦ “ጥሩ፡ ይህን በመሰማቴ ደስ ብሎኛል፡ እመቤት፤ ለእግዚአብሄር መንግስት ቅርብ ሳትሆኚ አትቀሪም።” እናም ላጥ ብላ ሄደች።

66 እዚያ የቆመች እሮጉት ነበረች። “እንዲህ ብየ፡ ሴትየዋን ታውቂያታለሽ? ” አልኳት።

“አዎን።”

“ትክክለኛ ክርስትያን ሳትሆን አትቀርም፡” አልኳት።

67 “ወንድም ብራንሃም፡ ዛሬ ሳትነካው ያለፍከው አንድ ነገር፡ ሐሜት ነው። እሷ’ኮ በአገር ደረጃ የሐሜት አለቃ ናት፡” አለች። ይሄው፡ ይሄ ነው፡ አያችሁ።

68 እንዲህ ዓይነቱ ነገር ላይ ስትመጡ ግን፡ ሰባኪው በመድረክ ላይ ያምጣው አያምጣው፡ እነዚህን ዓለማዊ የስጋ ነገሮች ሰታዩ፡ ምንም እንኳን ከነዚህ ነገሮች ጋር በትዕግሰት-ብትቆዩም፡ ከእግዚአብሔር የራቃችሁ ናችሁ፡ መንፈስ ቅዱስም ይሸሻል። ጉባኤዎች እንደ ጥንቱ የማይሆኑበት ምክንያቱ

ይህ ነው። በዚህ ቤተክርስትያን ዛሬ ማለዳ ብዙዎች በንስሀ የማይወለዱበት ምክንያቱ ይህ ነው። በአገሪቱ ዙርያ የድንኳን ሪቫይቫል የቀረበት ምክንያት ይህ ነው፡ ጨዋዋ የእግዚአብሔር ርግብ አሳዝነን ስላባረርናት። ትክክል ነው። መለያየት በመካከላችን እስካለ ድረስ፣ እስከተማማን ድረስ አብሮን አይቆይም፡ “የራሳችን መንገድ እስከፈለግን!”

69 አሁን እንድታስተውሉ ፈልጋለሁ፡ በጉ ዝምተኛ በግ ነበረ። መጽሐፍ ሲናገር፡ “እንደ በግ በሸላቾች ፊት፡ አፉን አልከፈተም፡ ዝም ብሎ ነበር።” አፉን አልከፈተም። መብቱን ፈላጊ ዓይነት ሰው አልነበረም። አይ፡ ጌታየ፡ መብቱን ለመተው ፈቃደኛ ነበረ እንጂ። ዝምተኛ በግ ነበር።

70 ዛሬ፡ ግን፡ ኦህ፡ ማይ፡ መለያየታችንን እንዴት እንደምንፈልገው! ኦህ፡ ማይ! “ልንገራችሁ፡ ብቻ አንድ ሰው እኔን የሆነ ነገር ይበለኝ፡ ሄጄ እይዘውና፡ የኔ ጌታ፡ እገነጣጥለዋለሁ።” “ቆይ ይህች ግብዝ ላገኛት እና አስማታለሁኝ! ቆይ ብቻ ላግኛት! ጌታ ይባረክ፤ ሃሌሉያ! ኡህ-ሁህ!” ርግቧ በርራ መንገዷ ትሄዳለች። ትክክል ነው። በእንዲህ ስሜት ውስጥ እስካላችሁ ድረስ፡ መንፈስ ቅዱስ አብሮአችሁ አይቆይም። በማስታወሻችሁ ጽፋችሁ ያዙ፡ ፈጽሞ አይቆይም። መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ዓይነት መንፈስ ባለበት ቦታ አይቆይም። የበግ ጠቦት መንፈስ፣ ጨዋ መንፈስ መሆን አለበት፤ ወይ ደግሞ ፈጽሞ አይቆይም፤ በመንፈስ ቅዱስ የተመራ፤ ጨዋና፣ ትሁት ካልሆነ፡ እሱ እንዲህ ነው። ምንም ነገር ቢመጣ እንኳን፡ ትዝም አይለው፡ ዝም ብሎ ይቀጥላል እንጂ። አያችሁ? ታውቃላችሁ፡ ፊታችሁን የምትመልሱባት ያቺ ደቂቃ፡ ያኔ... ዞር በምትሉበት ጊዜ።

71 የሐጢያት አጀማመር ሰው ለአንድ ደቂቃ ዞር በማለቱ እንደሆነ፡ ታውቃላችሁ። ታውቃላችሁ ወይ? መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ሰይጣን የሚለውን ለመስማት፡ ሄዋን ለአፍታ ብቻ ዞር አለች፤ እና እውነት እስኪመስላት ድረስ በጣም ቆንጆ ስዕል ሳለላት። እርሷም አዳመጠችው።

72 ዲያብሎስ ከእናንተ የሚፈልጋት ብቸና ነገር፡ ለጥቂት ደቂቃ ብቻ ዞር እንድትሉ ነው። እንዲህ በማለት ስዕሉን ይቀባባዋል፤ እንዲህ ይላል፦ “አሁን እይ። ታውቃለህ፡ ወንድም፡ ታውቂያለሽ፡ እህት፡ ትክክለኛ ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ፡ ይሄን **ባላደረጉ** ነበር። ታውቃለህ፡ እዚህ ቦታ **ይሄን** ካደረጉ።” ትክክለኛ እና እውነት እስኪመስላችሁ ድረስ እውነታ ሊያደርግባችሁ ይችላል። እውነት ነው! ነገር ግን አስታውሱ፡ ዲያብሎስ ነው!

73 ምን ያህል ቁልቁል-እንደወረዱ፡ የቱን ያህል በሐጢያት እንደተዘፈቁ እያሳሰበኝም፤ በእጆቻችሁ አቅፋችሁ በእግዚአብሄር ፍቅር ደግፋችሁ የማውጣት ግዴታ የእናንተ ነው። የእግዚአብሄር ርግብ ከረግረግ ጭቃ ደግፎ ያስነሳችሁ ጊዜ የት ነበራችሁ? ወዳጄ፡ ጉዳይህ ነው። ይቺ ዓለም ለትንሽየ ፍቅር ሲባል እየሞተች ናት። ያን...

74 ይሄኛው እንስሳም፡ እንድታስቡት እፈልጋለሁ፤ ይህ ታናሽ እንስሳ፤ በጣም ዝምተኛ በግ ነበር ምክንያቱ... እነሱ ሲዘነዝሩበት፡ መልሶ አልሰነዘረባቸውም። አልተቃወመም ወዲያ ወዲህ አላለም፣ አልጎረረም አልተንጠባረረም፡ ምንም አላለም። አንድ ሰው... ሲያጠቁት፣ መልሶ አላጠቃም። አፉን አልከፈተም።

75 እስኪ ወይ እኔን ወይ እናንተን አንድ ሰው ይበድለን፡ ኦህ፡ ማይ፡ ከጀርባው እንደተቀለበ እንቁራሪት ጉብ እንላለን፤ እንዳረጀች ዳክየ—እናባብጣለን። "በል ልንገርህ እሺ፤ ሁለተኛ እንዲህ ቢያደርገኝ፤ ወደዚያ ቸርች ፈጽሜ አልመለስም። አላደርገውም፡ እሺ! ጌታ ይባረክ! ሃሌሉያ! ናዝሪኖች ይቀበሉኛል፣ ፕሊግሪም ሆሊነስ፡ ይወስዱኛል። ሃሌሉያ። ይሄን ያህል አልታገሰም።" በጣም ጥሩ፡ ርግቧ ትበርራለች።

76 "ታውቂያለሽ? ያቺ ግብዝ ወደዚህ ቸርች የምትመጣ ከሆነች፡ ደግሜ አልመጣም። ጌታ ይባረክ፡ ፈጽሜ አላደርገውም!" በዚያ ያረጀ አጉረጥራጭ ተኩላ፤ ስትጠቁ፤ ርግቧ ትበርራለች። ትክክል። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ሄዷል ማለት ነው።

77 ከዛ በኋላ ምን ሆኛለሁ ትላላችሁ። ቤተክርስትያን ምን ነካት ትላላችሁ። ምን ነካኝ ትላላችሁ። እንደ ድሮየ ድል የማልነሳው ለምንድነው? ተፈጥሮህን ቀይረህዋል። በግ ከመሆን ይልቅ ፍየል ሆነሃል። የበግ ጠቦት ከመሆን ሌላ ነገር ሆነሃል።

78 ያንን እውነተኛና ትሁት መንፈስ ይኑርህ፡ "መንፈስ ቅዱስ የትም ይምራኝ። ጌታ ሆይ፣ የትም ቢሆኑ፣ ኃጢአተኞችን ሁሉ እወዳለሁ።" በሰዎች ልብ ውስጥ እንዲህ አይነቱ ሰፍራ ብቻ ይገኝ፡ ያኔ ነፍሳችሁ ውስጥ፤ አንድ ነገር ሲሆን ታያላችሁ።

79 "መልካም፡ ወንድም ብራንሃም፡ ለዚህ የሚሆን መፍትሄ ይኖር ይሆን? " ብትሉ። አዎን፡ በግ ብቻ መሆን ነው፡ ሌላ የለውም። "እሺ፡ ወንድም ብራንሃም!" ትላላችሁ፤

80 ባለፈው ማታ በሽሪቬፖርት፡ አንዲት ወጣት ሴት ጋር ተዋወቅኩ። ጉባኤው ካለቀ በኋላ እኔ እና ቢሊ ሳንድዊች ለመብላት ወደ አንድ ሰፍራ ወጥተን ነበር። ቆንጆ ወጣት እናት መጣች፡ ምናልባትም ወጣት ሴት፡ ምናልባት ሀያ ወይም ሀያዎቹ ክልል፡ በደንብ የለበሰች። ቁጭ አለችና። ወደዛ ደጋግማ ስትመለከት አስተውያት። መብላቴን ቀጠልኩ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንዲት ወይዘሮ መጣች። "እንዴት ናችሁ? " አለች። ተነጋገርን። ወይዘሮዋ እህት ዴቪስ እንደነበረች አውቄያታለሁ። እሷና ከላይፍ ተበርናክል ሌላ እመቤት፡ በደንብ አውቃቸዋለሁ፡ መጥታ አነጋገረችኝ፡ ተመልሰው ሄዱ። ከዛ በኋላ ማዶ ላይ የተቀመጠችው ወጣቷ እመቤት፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ዛሬ ምሽት ደሰ የሚል መልዕክት ነበር፡" አለችኝ።

81 እኔም አልኳት፦ "ጤና ይስጥልኝ፡ እህት? " "በጣም፡ አመሰግናለሁ፡" አልኳት። ደግሜም፦ "የላይፍ ተበርናክል አባል ነሽ? " አልኳት።

82 "አዎን ነኝ፡" አለች። እና እንዲህ አለች፦ "ታውቃለህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ በኳየር መዘመር እችል ነበር፡ ነገር ግን ክልከላዎችን ያደርጋሉ።" "ኦህ፡ ብዙ ዓመታት፡ የቮካል ልምምድ አድርጌአለሁ፡ እንዲህ እና እንዲያ፡" አለች። "ሶሎ እዘምራለሁ እንዲሁም ሌሎች ዓይነቶች እዘምራለሁ፡" አለች። እንዲህ አለች፦ "እኔ—ግን፤ ብዙ ክልከላዎች—ስለሚያበዙ መዘመር አልቻልኩም 'ቀለም የተቀባባች ሴት—በኳየር አትዘምርም።' ይላሉ።"

እኔም፡ "በጣም ጥሩ፡ እግዚአብሄር ይባረክ ስለ ላይፍ ተበርናክል!" አልኳት።

83 እንዲህ አለች፦ “እሺ፥ ልንገርህ፡ ወንድም ብራንሃም” ፣ “እኔ ክርስትያን ነኝ።” አለች።

84 “ስለዚህ፡ እህት፡ ወደቤትሽ ሂጂና ፊትሽን ታጠቢ፡ ወይም ማድረግ ያለብሽ አርጊ፤” አልኳት። እንዲህ አልኳት፦ “ፊትሽ ላይ ያንን ርካሽ አሸንክታብ እንደ ሸፋን እቀባለሁ ነው የምትይኝ… ”

85 ከሰይጣን የመጣ እንደሆነ ላረጋግጥልሽ እችላለሁ። ውስጡ ምንም ነገር እንደሌለ ላረጋግጥልሽ እችላለሁ… መነሻው የአሕዛብ ነው። አንቺም እስከተቀባባሺው ድረስ፤ የአሕዛብ ምልክት ነው። እኔ አሁን፡ ከአፍሪካ መምጣቴ ነው፤ የጆሮ ጌጥ እና ሌሎች ከሚገኝበት በሆተንቶት ጫካ ውስጥ ነበርኩ፡ በጆሮ ላይ እና በአንገታችሁ ዙርያ የሚጠቀለሉ ብዙ ጌጣጌጦች አሸንክታቦች፡ እነዚህ ሁሉ፡ የሚመጡበት፤ እነዚህ የሚመጡበት ሰፍራ ነበርኩ። የአሕዛብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስትያኖችን እንደ አሕዛብ እንድንሆን አይፈልግም። አንቺም አያስፈልግሽም… ይሄን ስላደረግሽ አሕዛብ ነሽ ማለቴ አይደለም፤ ራስሽን ግን ከነሱ እንደ አንዷ እያስመሰልሽ ነሽ። ፓስተራችሁ እውነቱን ስለማይነግራችሁ ብቻ ነው። መጽሀፍ ቅዱስ ይላል።

86 አሁንም እንዲህ ትላላችሁ፦ “ወንድም ብራንሃም፡ ጸጉሬን ካሳጠርኩት፡ የሚያምርብኝ ይመስለኛል እንዲህ እንዲያ።” አዎን ትክክል ነው፡ ነገር ግን ረዥም ጸጉር ቢኖርሽ የበለጠ ውብ ትሆኛለሽ። አንገትሽን ሁሉ ዞሮ፡ ይሸፍንልሽ እና ትክክል ያደርግልሻል።

87 ለምን፤ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ታውቃላችሁ? አንዲት፡ ሴት ጸጉሯን ከቆረጠች ባልዋ ከሷ ሊርቅ እና ሊፈታት መብት አለው። ጸጉራ ከቆረጠች፡ ለሱ ታማኝ ሳትሆን እየኖረች እንዳለች ያሳያል። መጽሐፍ ቅዱስ ብሏል፡ አንደኛ ቆሮንጦስ 12፡ መርምሩት እውነት ካልሆነ። እሷ… ጸጉሯን የምትቆርጥ ሴት ራሷን ታዋርዳለች፡ ባልዋን ነው። አዋራጅ ከሆነች፡ መፈታት እና መራቅ አለባት። ይህ እውነት ነው። ግን፡ እያችሁ፡ ፓስተሩ እነዚህን እውነቶች ፈጽሞ አይነግራችሁም። የምታደርጓቸው የምታደርጉበት ምክንያት ይህ ነው። እናም—— እንዲሁም ስለ ወንዱ፡ መጽሐፍ ሲናገር…

88 በቅርብ ጊዜ አንድ ሰው ጽፎ እንዲህ አለኝ “ወንድም ብራንሃም፣ እነዚያ—— የሴቶች ሹራቦች፡” “ለምንድነው፡ ይሄን ያህል… አሁን አሁን ሹራቦቹ ፍጹም አይገኙም፤ ለእኛ ክርስትያን ሴቶችስ እነዚያን ሸፎኖች እና ናይለኖችን ወይም እንዲያ የመሳሰሉት መልበሱ መልካም ነው ወይ? ”

89 እንዲህ አልኳት፦ “ይሄውልሽ፡ እህት፡ አንድ ነገር ብቻ ማድረግ ነው። አንድ እውነታ አለ። ይሄን ማድረግ ትችያለሽ፡ መግዛት ካልቻልሽ፡ የልብስ ስፌት ማሽኖች ይሸጣሉ፤ ማዘጋጀት ትችያለሽ።” “ትክክል ነው። ልከኛ ለማስመሰል… ” አልኳት። ታውቃላችሁ፡ እራሱን ገልጦ የሚወጣው በልብ ያለው ነገር እንደሆነ… አምናለሁ። አኳኋን እና አደራረግ፡ በውስጥ ያለውን ነገር የሚያሳይ ነው።

90 እነዚህ ሁሉ የሚቆጡ ቅጥ እያጡ እና የሚያሙ፤ እና——እና የሚደባደቡ፤ ምክንያታቸው ይህ ነው፤ በቸርች ዙርያ የሚዞር ሁሉ፤ ቤተክርስትያንን የሚያፈራርስ ይህ ነው። መንፈስ ቅዱስ ጥሎአችሁ እንድሄደ፡ ዲያብሎስ ግን በውስጣችሁ እንዳለ ያሳያል። አሁን ከአንዳንዶቻችሁ፤ ሰሙን አንገብግቦ

እያወጣላችሁ እንዳለ አውቃለሁ፤ መሆን ግን አለበት። መሆን አለበት! የተነገረበት ምክንያት ለዚሁ ነውና፤ አሪፍ ለመሆን፣ ግሩም አክት ለማድረግ ሳይሆን፦ ችግሩ የቱ ጋር እንዳለ ለማሳየት ነው፤ ምክንያቱ እኔም አንድ ቀን ስለ እናንተ መልስ ለመስጠት መቆሜ አይቀርምና። ስለዚ አንድን ነገር የምትከውኑበት እና የምታደርጉበት ዋና ምክንያት፡ ማን መሆናችሁ ያሳያል። በትንሽ ነገር እጀታን የሚያሰወረውር የቆየ ቁጣ ካለባችሁ፡ እዚህ ወጥታችሁም ከቀጠላችሁበት፡ ወይም ነቃፊነት፣ ተሳዳቢነት የመሳሰለ ነገር ካለባችሁ፣ ከየት የመጣ መሆኑ ያሳያል።

91 አሁን ማድረግ የሚቻለው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ይህ ነገር ከእናንተ አስወግዱ፡ ርግቡ ወደ ልባችሁ ይመለሳል። ርግቧ ከመርከብ ስትሄድ፡ ተዘግቶባት ነበር። ስትመለስ ግን መጥታ ኖህ እስኪያስገባት ድረስ በመርከቡ በር አንኳኳች። [ወንድም ብራንሃም ፑልፒቱ ላይ አምኳኳ—አርታዒ።] መንፈስ ቅዱስ እዚህ አለ። መንፈስ ቅዱስ መግባት ይፈልጋል። ዛሬም መንፈስ ቅዱስ፡ ከእናንተ ለዘላለም ያልራቀበት ምክንያት፡ ይህ ነው። ወደ እናንተ በርሮ ለመመለስ እና ለመግባት፡ ከዛፍ ቅርንጫፎች መካከል በአንዱ ላይ ቁጭ ብሎ፡ ድሮ የነበራችሁ ሰላም እና ደስታ እንዲሰጣችሁ ተዘጋጅቷል። በትክክል፡ ነው። ይህ ለማድረግ ዝግጁ ነው። ሊያደርገው ይፈልጋል። ይህ ለማድረግ ይናፍቃል። እናንተ ግን አታስደርጉትም!

92 አሁን የምናገረው፡ ለእናንተ ለእንግዶች አይደለም። እኔ ፓስተራችሁ ምንነቱን አላውቅም… እኔ የምናገራቸው የብራንሃም ተበርናክልን ነው። የምናገረው ከሌላ ቸርቾች ላላችሁ ሰዎች አይደለም። ንግግሬ ከብራንሃም ተበርናክል ጋር ነው። እዚህ ዙርያ ላይ ያለው ችግር ይህ ነውና።

93 ርግቧ እንድትበርር የሚያደርጋት ነገር ይህ ነው። ብቻ አንድ ሰው በቸርች አከባቢ አንዳች ነገር ይጀምር፤ የመጀመርያው ነገር፡ "ኦህ፡ ተባለ'ዴ? ኦይ፡ ነው… ? አትለኝም? " ያኔ ወድያውኑ መንፈስ ቅዱስ፡ በርሮ ይሄዳል። እሱ ይህን አይነት መንፈስ አይታገስም። የበጉ ተፈጥሮ ከእናንተ እስከራቀ ድረስ፣ መነፈስ ቅዱስ ይሄዳል። እውነት ነው። ዛሬ ያለው ችግርም ይህ ነው። ህዝቡ አሁን ወዳለበት ሁኔታ ያደረሰው ምክንያት ይህ ነው፣ ምክንያቱ የተሳሳተ መንፈስ ወደ ልባቸው፡ እና ወደ ህይወታቸው እንዲገባ ስለሚፈቅዱለት። እኛም የተያዝንበት ምክንያት ይህ ነው…

94 መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር በመካከላችን ብዙ የታመሙ እና የተኀሳቀሉ የመኖራቸው ምክንያት፡ ይህ ነው ይለናል። ርግቡ በእኛ ውስጥ መኖርያ እንዲያደርግ፡ በግ መሆናችን ግድ ነው። ጨዋ መሆን አለብን። ሰላማዊ መሆን አለብን።

95 አሁን፡ አትርሱ፡ ርግቡ ይመጣል። እንዲህ ይላል፤ "ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ መንፈስ ቅዱስን ፈጽሜ ተቀብየ አላውቅም በለኛ። ሃሌሉያ! ያኔ ማታ፡ እንዲህ እየተመላለስኩ፤ አንድ ቀን ማታ ላይ፡ ኦህ፡ እሱ መጣ… " አዎን፤ እሱ ነበር! "ኦህ፡ በጣም ደስታ ተሰማኝ፡ እያንዳንዷ ወፍ ከዛፍ አውርጄ ማቀፍ እና ማፍቀር እንደምችል ተሰማኝ። እኔን ክፉኛ የበደሉኝ እጅግ ክፉ ሰዎችን፤ ክንዶችህን ጣል አርገህ እቀፋቸው ተሰማኝ። ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ እቤት ያኔ የተሰማኝ!" አዎን፡ መንፈስ ቅዱስ ነበር።

96 ግን፡ አብርሆ ያልቆየበት ምክንያት፡ አይተሀዋል። ያኔማ በግ ነበርክ፤ ተኲላ ከሆንክ በኋላ ግን፤ በርሮ መሄድ ነበረበት። እናንተ ናችሁ እንጂ፡ ርግቧ ጋር——ምንም——ምንም ችግር የለም፡ እና ደግሞ... ያንን መንፈስ እንዲገባባችሁ ትፈቅዳላችሁ። “እኔ ነኝ ያስገባሁት፡ ወንድም ብራንሃም? ” አዎን፡ ሐሜት ለመስማት፣ ውሸት ለመስማት ዞር ባላችሁ ጊዜ፤ “አዎን፤ መብት አለኝ!” ለማለት ስትሄዱ።

97 ምንም መብት የላችሁም! በዋጋ ተገዝታችኋል፤ ዋጋውም ውድ የእግዚ አብሄር ልጅ ደም ዋጋ ነው። ምንም ዓይነት ህጋዊ መብት የላችሁም። ሃሌሉያ! ይቀረላችሁ ብቸኛ መብት፡ ከአማኑኤል ደም ስር ወደ ሚፈሰው ምንጭ መጥተው፤ ሐጢያተኞች ከደሙ ስር ወድቀው፡ የጥፋት ዝገት እንደሚያሰወግዱ፡ መምጣት። አዎን፡ ወዳጄ። የቀረላችሁ ብቸኛ መብት፤ የራስ-ፈቃድ፤ ለእግዚአብሄር ማስገዛት፡ ከዛ በኋላ እግዚአብሄር ይመራል። ጉባኤዎችን የሚመራው እንዲሁ ነው... በዚህ መንገድ ነው ብዙ እንግዳ ነገሮች የሚሆኑት። መንፈስ ቅዱስ ወድ አንድ ቦታ ይሄድና፡ ከዛ መንፈስ ቅዱስ፦ “ይህ ትክክል አይደለም። ጉባኤውን አቁምና፡ ወደፊት ቀጥል” ይላል። እኔም፡ አቆማለኋ፡ ወንድሜ፡ ወደ ፊት እቀጥላለሁ። ምክንያቱ በእግዚአብሄር መንፈስ መመራት አለባችሁ፡ ትክክል። በእግዚአብሄር መንፈስ ለመመራት ብቸኛው መንገድ፡ ብዙ ነገር በማወቅ አይደለም፡ ጨዋ በመሆን ነው።

98 “ኦህ፡” “ብዙ የማውቅ” ይመስላችኋል። አዎን፡ አእምሯችሁን ከጥግ እስከ ጥግ ታስሩታላችሁ ግን ራሱ እንኳን አያበጅም። መጻሕፍት እና መልሶቻቸው ሁሉ፣ ግሪክ እና ዕብራይስጥ ሁሉ ታውቃላችሁ፤ ርግቧ የምታርፍበት ስፍራ ግን አይገኝበትም። እውነት ነው። ሁሉንም ታውቁታላችሁ፤ ብዙ ስለምታውቁ፡ ርግቧ መምራት አትችልም።

99 በግ ይሄን አውቃለሁ አይልም። የሚመራው ሌላ ሊኖር ግድ ነው። ክብር! ይሄው ነው። ምንም አላውቅም! አሜን። እኔ የማውቀው አንድ ነገር፡ ክርስቶስ ኢየሱስ፡ እኔን ለማዳን መሞቱ ነው።

100 ወደ ካሊፎርኒያ የሚወርድ አንድ ሰው፡ ከፊቱ አንድ ምልክት ነበረው፡ “እኔ የክርስቶስ ሞኝ ነኝ፡” ከኋላው ደግሞ፡ “አንተስ የማን ሞኝ ነህ? ” የሚል ምልክት። ልክ ነው። መንፈስ ቅዱስ እንዲመራችሁ፡ ለዓለም፡ ሞኞች ሁኑ፡ ምክንያቱ የእግዚአብሔር ሴቶች እና ወንዶች ልጆች የሚመሩት በመንፈስ ቅዱስ ነው። ሮሜ 8፡1፣ እንዲህ ይላል፡ “በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኲነኔ የለባቸውም፡ በመንፈስ እንጂ፡ በስጋ ፈቃድ የማይመላለሱ” እንደ ርግቧ እንጂ፡ እንደ ተኲላው የማይመላለሱ። አሜን።

101 ዶክ ሲዘምር “ከሰማይዋ ርግብ ጋር ሰጓዝ፡ ዘወትር መንገዴን በፍቅር ይሙላው፤ ይል ነበር፤ በመዝሙር እና በፈገግታ ይህን ሁሉ ሰሄድ፤ ዘወትር መንገዴን በፈቅር ሙላ።” ለብራንሃም ተበርናክል ይሁን፡ ለሌላ ቤተክርስትያን ወይም ለግለሰብ፡ በግ ለመሆን መብታቸውን ሲሰውት፡ ልዩ የሰላም ቀን ይሆናል።

“ጥያቄው ምንድነው፤ ወንድም ብራንሃም? ”

102 በግ ወደ መሆን ተመለሱ፡ ወደ ጨዋነት ተመለሱ፣ ምንም የማታውቁ ሁኑ፤ እራሳችሁን ለክርስቶስ ለማቅረብ ተመለሱ። ምንም ለማወቅ አትሞክር፡

አትሞካክሩ። ብቻ በትሕትና፣ በዝግታ፣ በየዋህነት፣ በጨዋነት ተመላለሱ፡ ርግቡ ይመራችኋል። ግን የምታዩትን ሁሉ... ሐሜት ለመስማት ስትሄዱ፣ ያንን ቁጣን ለመቀስቀስ ስትወጡ፣ ይሄን እና ያንን ለማድረግ መብት አለኚ ብላችሁ ለማሰብ ስትጀምሩ፣ ርግቧ በርራ መንገዷን ትቀጥላለች። ከዛ በኋላ አብራችሁ የለችም። ቤተክርስታን ሆይ፤ አሁን በዚህ ማለዳ ከእናንተ አልራቀችም። በሰላም ቅርንጫፎች ላይ ቁጭ ብላ፡ የእናንተን ተፈጥሮ ለውጥ እየተበቀች ናት። አሜን።

103 ዛሬ ከእናንተ የሚጠበቀው መብቶቻችሁ ሁሉ ማስገዛት፣ እግዚአብሄር እናንተን ጥሎ መብቶቻችሁ ሁሉ ከእናንተ ላይ እንዲሸልት መፍቀድ ነው። አሜን። በበጉ—ላይ የተሰቀለውን ከፊይ ሁሉ ስታስቡት አይገርማችሁም? መብቱ’ኮ ነው። አዎን። “ህ፣ ህ፣ ህ።” ሃሩር ይሆንበታል፡ ከዛ በኋላ ወደ ሚሸለትበት ጠረጴዛ ያስተኙታል። ምን እንደሚሻለው ያውቁለታል። መብቱን ሁሉ ከላዩ ሸልተው ሲወስዱለት፡ እንዴት ቀሎት እና አምሮበት እንደሚሮጥ። ማይ፡ ማይ፡ ደስ ይለዋል፡ ብዙ ጊዜ ሰላለው ይቦርቃል። አዎን፡ ወዳጄ። መብታችሁን ብትተው፡ የሚሆንላችሁ ይህ ነው። ግን መብቶቻችሁን ሁሉ በመተው የእግዚአብሄር ቃል ዓለምን ከእናንተ እንዲሸልት መፍቀደ አለባችሁ፣ ዓለማዊ ልምዶች ሁሉ እንዲወሰድላችሁ፡ ከዛ በኋላ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ትሆናላችሁ።

104 ቆይተዋል የሆነ ጊዜ ነው፤ አፍሪካ ላይ፤ ከአንድ ቅዱስ ሰው ጋር—እያወራን ነበር። ሲናገርም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ መለኮታዊ ነገር እንደምታምን አውቃለሁ’ አለኚ።

“በደንብ፤ ወንድሜ፡” አልኩት።

105 እሱም፡ “ከዓመታት በፊት እራሴን እንደ ልዩ ሰው አድርጌ እቆጥር ነበር።” “እውነተኛ ክርስትያን ነኚ ብየ አሰብ ነበር፡” አለኚ። ከዛ እንዲህ አለ፤ “ከዛ በኛ ቸርች... መኪናየን ባቆምኩበት በኩል፤ የሆነ ተራራ መውጣት ነበረብኚ።” አለኚም፡- “ኦህ፡ ሶስት ወይ አራት መቶ ያርድ፡ ያህል ተራራ መውጣት ነበረብኚ፡ እሱም ወደ ላይ ለመውጣት፡ ጥሻዎች እና የተለያዩ ነገሮች እያቋረጥኩ።” “በተራራው ላይ የጸሎት ሰብሰባ ስለነበረብን፡” ይላል። “እና ስለ ራሴ ልዩ ክርስትያን ይመስለኚ ነበር፡” አለ። እንዲህ አለ፡- “ሙሉውን መጽሀፍ ቅዱስ አውቀዋለሁ። ዕብራይስጥ ሁሉ አጥንቻለሁ። የቃላት ትክክለኛ አነጋገር ዘየ ተምሬአለሁ።” አለም፡- “ማንም ወደኔ ቢመጣ፤ በደንብ” [ወንድም ብራንሃም ጣቱን አንቃጨለ—አርታኢ።] “ስለመጽሀፍ ቅዱስ ሳናግራቸው። ስለማወራው ነገር በደንብ አቃለሁ።” እንዲህ አለ፡- “ስለዚህ አንድ ቀን ማታ ወደ ቸርች እየሄድኩ። በቸርቻችን ብዙ አለመግባባት ነበረና።” አለ፡- “አንደኛው ከሌላ ጋር የሚጠላላ ትንንሽ ቡድኖች ነበሩ። እንዴት እንደሚያድጉ አንተም ታውቀዋለህ።”

“አዎን፡ ትክክል፡” አልኩት።

106 እንዲህ አለ፡- “ወደ ተራራው ለመውጣት፡ መንገድ ላይ ሰራመድ፡ እንደ ድንገት ሰው እየተከተለኚ እንዳለ አይነት መረዳት ውስጥ ገባሁና።” እንዲህ አለ፡- “እስኪ ማን ይሆናል ጥቂት ልጠብቀውና፡ እግረ መንገዳችን ለመነጋገር፡ ልገናኘው ብየ አሰብኩ።” ታውቃላችሁ፤ እንዲህ አይነቱ ነገር፡ ጥቂት መታገስ

መልካም ነው። እና ሲናገር፦ “ተራራውን እየወጣሁ ሳለው፡” እንዲህ ይላል፦ “ወደ ላይ ወጣሁና። አንድ ሰው ዳገቱ ላይ ብቅ አለ፡” “ጀርባው ላይ ሰውየው ከሱ ይልቅ የገዘፈ ሻንጣ ተሸክሞ ነበር” ይላል። እና፡ “ዳገቱን ለመውጣት፡ በአጭር እየተራመደ፡ እያለከለከና እየቃሰተ ይሄድ ነበር። እኔም፦ ‘ጓደኛ፡ ይህን ጭነትህን ዳገቱ ጋር ለማድረስ ላግዝህ?’ አልኩት፡ እሱም፦ ‘አይ፡ የግድ ማውጣት አለብኝ፡’” አለኝ። “እና እጁን ሳየው፡” አለ። “እጁ ላይ ጠባሳዎች ነበሩት። ስለዚህ ራእይ እንደሆነ አወቅኩ፡” አለ። “አፈርኩና፡ ‘ጌታ ሆይ፡ በሻንጣው ላይ የምትሞላው ነገር የዓለም ሐጥያት ነው?’ አልኩት፡ እሱም አለኝ፦ ‘አይደለም፡ የምሞላው የአንተ ነው። አንተ እንድትቀጥል፡ ዳገቱ ላይ እያደረስኩህ ነው።’”

107 ነገሩ እንዲሁ ነው። ዙርያችንን ዞር ብለን ብናይ፡ ጓዞቻችንን እየሰበሰበልን እንዳለ እናስተውላለን። ትንሽነት አይሰማችሁም? ምክንያቱ ማድረግ እየተቻለን፡ ይህ ክፉ እና ጨካኝ ልባችን!

108 እንደምታውቁት አደን እውዳለሁና፡ የሆነ ቀን እዚህ እያደንኩ ነበር። ከተማው ላይ አንድ ክፉ ሰው ነበረ፡ ክፉ ጓደኛ ነው። ሴት አጋዘን ላይ እና ጠቦቶች ላይ መተኮስ አልፈልግም “እጅግ ዘግናኝ ነው” ስለምለው፡ ይቀልድብኛል። እንዲህ ስለው፦ “አርጅተው ለመሞት የተዘጋጁ ስለሆኑ፡ ዕድሜአቸው ክፍ ያሉት ላይ ተኩሰህ፡ ለምን ትክክለኛ፣ እና ንጹህ አዳኝ አትሆንም? እግዚአብሄር እነሱን ለኛ ሰጥቶአቸዋል። እባክህ እነዚህ ወጣት እናቶች እና ሌሎች... ”

109 “አይ፡ አንተ ድግሞ የደሮ-ልብ፡ የሆንክ ሰባኪ ነህ!” እያለ፡ ይደጋግምብኛል።

110 እኔም፦ “ይሄውልህ፡ አሁን ቢርበኝ፡ እና የአጋዘን ጠቦት ቢያምረኝ፡ እግዚአብሔር እንደሚፈቅድልኝ አምናልሁ። አሪፍ ለመባል መተኮስ ግን፣” ስለው፡ በቃ ካርታውን ሞልቶ። ሄደና ፋጨት በሚመስል መልኩ፡ ጠራው፣ እና ፋጨቱን ሲያሰጮህ ልክ የአጋዘን ጠቦት ጩኸት ያስመሰለዋል። አንድ ቀን ጫካው ላይ አብረን ነበርን። “እኔ በራሴ አፍራለሁ፡” ብየ፤ እንዲሸማቀቅ አደረግኩት። አሪፍ ለመባል ብቻ፡ ጠቦቶቹን እና ሌሎቹን ጨምሮ ከቻለ፡ ስምንት ወይም አስር በአንዴ ይረፈርፋቸዋል፣ ያውም'ኮ የተወሰነው አካላቸው ቆርጦ ሌላው ሊተወው ነው። “ማድረግ የለብህም፡” አልኩት።

“አይ” ፣ “እናንተ ሰባኪዎች ግን ልበ-ደሮዎች ናችሁ!” አለ።

111 አንድ ቀን ጫካ ውስጥ ተደብቆ፤ የተለመደውን ፋጨት አድርጎ ጮኸ፣ ድምጹም የአጋዘን ጠቦት ድምጽ ይመስላል። ልክ ይሄን ሲያደርግ፤ ውብ ሴት አጋዘን እየዘለለች ጭንቅላቷን ብቅ አደረገች። ትልልቅ ቡናማ አይኖቿ እዚህ እዚያ ሲያዩ ይታያሉ። ተደናግጣለች። ዙርያውን ታያለች። አዳኙ ዝቅ አለ፡ እናት አጋዘን ለመግደል ጠመንጃውን ከፍ አደረጋት። አጋዘኗ አዳኙን አየችው። ምን እንደሆነ ግን ታውቃላችሁ፡ በጠቦቱ ጩኸት፡ ጠመንጃውን ትዝ አልላት አለ። ችግር ውስጥ ስለገባ፡ ጠቦቱን ትፈልገዋለች። ታውቃላችሁ፡ ትክክለኛ እናትነት እና የእናት ፍቅር፡ የጠመንጃውን አፈሙዝ እያየች፡ ለመሞት፡ ግንባሯን ለጠመንጃ፤ እንደሚያሰጥ ያሳያል። ታውቃላችሁ፤ ሁኔታው እጅግ ድንቅ ከመሆኑ፡ እሱ ድረስ ተጠጋችና፡ ትዕይንቱ ጠመንጃውን አስጣለው!

እየሮጠ መጣና ክንዴን ያዝ አርጎ፡ “ቢሊ፡ ጸልይልኝ፡ በቃኝ ይሄ ነገር!” አለኝ። ያንን የእናት ጀግንነት ሲያይ ነው!

112 ኦህ፡ ዓለም በእኛ ውስጥ፣ በሰው ልጆች ልብ ውስጥ የጀገነ የእግዚአብሄር ፍቅር ተገልጦ ማየት ስትችል፤ ልዩ ነገር ይሆናል። የእግዚአብሄር ርግብ ወደ ልባችን አስገብተን ጨዋዎች፣ እና ትሁታን ሲያደርገን ነው።

113 ወድያው እዚያው ጥላ ስር፡ ቆሜ ለወጣቱ ጸለይኩለት፤ ጌታ እንዲቀበል አደረግኩት። ከዚያ ቀን በኋላ፡ መልካም፣ እና ንጹህ አዳኝ ሆነ።

114 አዎን፡ ማረግ የፈለገውን ሁሉ ለማድረግ፡ መብት ያለው መስሎት ነበር። “እነሱም፡ ሲያስፈልጋቸው በማሳየ ገብተው ጥራጥሬዎቼ ይበሉብኛል።”

115 እኔም አልኩት፡- “አዎን ትክክል፡ ይሄን ማድረግ ግን ስብአዊነት አይደለም።” መብቶቻችሁን መተው አለባችሁ። ጌታ ሆይ፡ እንችል ዘንድ፡ እርዳን።

116 ኦህ፡ እዚህ ውስጥ ድሮ፡ የዛሬ መቶ ዓመት ገደማ፤ በዩናይትድ ስቴትስ ደቡባዊ ምዕራብ የሚኖር ታላቅ ክርስትያን ነበረ። ዳንኤል ከሪ ይባላል፤ ወርቅ የሆነ፣ የእግዚአብሄር ሰው፣ ቅዱስ ሰው፡ ሰው ሁሉ የሚመኘው ዓይነት ሰው፣ ትክክለኛ ክርስትያን፣ እንዲህ ዓይነት ሰው ነበር። እና ታሪኩ፡ በሞት ወይም በህልም እና በውን መካከል እንደሆነ፡ ሲናገር… በሞት፡ ሳይሆን አይቀርም፡ ወደ ሰማይ ተወሰደ። እና በዕንቁ ወደ ተሰራው በር ሲጠጋ፡ በር ጠባቂው ቀረብ ብሎ፡ “ማን ነህ? ” አለው።

117 እሱም፡- “እኔ ወንጌላዊ፡ ዳንኤል ከሪ ነኝ፤ ብዙ ሺ ነፍሳት ወደ ክርስቶስ ያመጣ ነኝ። እና… የምድር ጉዞየ ስላበቃ፡ ሌላ መሄጃ የሌኝም። ዛሬ ማለዳ መግባት እፈልጋለሁ።”

118 አንተ ሐጥያተኛ ሰው፡ አንዲት ማለዳ ወደ አንተም እንዲህ ትደርስብሃለች። ወደ ኋላ ለምትሉም፡ እንዲህ ትመጣባችኋለች። ጨዋ እና ቸር ባለመሆናችሁ መንፈስ ቅዱስን ለምታሳዝኑ፤ እንዲህ ትመጣባችኋለች። ለዓመታት ሳታለቅሱ ኑራችኋል። ለምን ያህል እንደሆነ ባላውቅም፡ ማፈር ትታችኋል። ልከኛ መሆን ከእናንተ ርቋል። አዎን። ከማለዳዎች አንዷ ግን ወደ በራችሁ ትመጣላችኋለች። ታድያ ጨዋው መንፈስ ቅዱስ ሲያንኳኳ፡ እንዲገባ ለምን አትፈቅዱለትም?

119 ስለዚህ ዳንኤል ከሪ—ወደ—በሩ በመጣ ጊዜ፡ ወደ ውስጥ ገቡና፡ “ስምህ መዝገብ ላይ ከሰፈረ እናያለን፡” አሉት። ዙርያውን ፈተሹ፤ ሰሙን ማግኘት አልቻሉም። “አይ፡ ዳንኤል ከሪ እዚህ የለም፡” አሉት።

120 “ኦው፡” “እርግጠኛ ነህ!” አለ፡ “እኔ’ኮ ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ አምጥቼአለሁ” አለ። አለም፡- “ትክክለኛ ነግሮችን ለማድረግ ጥሬአለሁ።”

121 በረኛውም፡- “ይህን በማለቴ አዝናለሁ፡ ዳንኤል ከሪ ግን እዚህ የለም ጌታየ፡” አለው። አለውም፡- “የምታደርገውን ልምከርህ።” “እኛ የአንተን ጉዳይ ለመፍታት እዚህ መብት የለንም፡” አለው። “ጉዳይህን ይግባይ ማለት ትፈልጋለህ? የምትፈልግ ከሆንክ፤ በነጩ ዙፋን ፍርድ ይግባኝ ማለት ትችላለህ፡” አለው። እዚህ ግን፡ “አንተ ስለሌለህ፤ ለአንተ የሚሆን ሞሕረት፡ ፍጹም፡ የለንም። ለአንተ የሚሆን ምህረት የለም።” “ይግባኝ ማለት ትፈልጋለህ? ” አለው፡

እሱም፡- “ጌታየ፡ ይግባኝ እላለሁ ኣንጂ ሌላ ምን ምርጫ አለኚ? ” አለ።

122 እሱም አለው፡- “እንግዲያውስ፡ ወደ ነጭ ዙፋን ፍርድ ሂድ እና፡ ጉዳይህ በዚያ ይግባኝ በል።”

123 ዳንኤል ከሪ ለአንድ ሰዓት ያህል በህዋ እንደሚሄድ ይሰማኝ ነበር ይላል። እሱ ሲናገር፡ ርቄ በሄድኩ ቁጥር፡ እየበራ ይሄዳል። እየበራ፣ እየበራ፣ እየበራ፣ እየበራ፣ ወደ አንድ ሰፍራ ደረሰ። ጸሀይ ከምታንጸባርቀው ብርሃን ይልቅ፡ በመቶ ጊዜና፣ በሺዎች ጊዜ እጥፍ ደማቅ ነበር። መንቀጥቀጥ ያዘኚ አለ፤ ተንቀጠቀጠ። ሲናገርም፡ ወደ ብርሃኑ መሐል በገባ ጊዜ፤ ከብርሃኑ ውስጥ—የወጣ፡- “በምድር ሳለህ ፍጹም ነበርህን? ” የሚለው ድምጽ ሰማ።

እየተንቀጠቀጠ፡ “አይ፡ ፍጹም አልነበርሁም፡” አለ።

“ከሰው ሁሉ ጋርሰ ቅን ነበርክ? ” አለው፡

124 (ሲናገርም፡- “ቅን ያልሆንኩባቸው ጥቂት ነገሮች ወደ ልቤ መጡና፡”) “አልነበርኩም፡” አለ። አለም፡- “አይ፡ ቅን—የነበርኩ—አይመሰለኝም።”

“በሕይወት ዘመንህ፡ በእያንዳንዱ ጉዳይ እውነት ተናጋሪ ነበርክ? ” አለው።

125 “አይ። አጣራጣሪ ያልሆኑ... አጠራጣሪ የሆኑ ነገሮች እንደተናገርኩ አስታውሳለሁ። እኔ—እኔ—እኔ—ፍጹምና ታማኝ አልነበርኩም።”

126 አለውም፡- “ሌላውስ፡ የአንተ ያልሆነን ነገር፣ ገንዘብ፣ ወስደህ ታውቃለህ፡ የአንተ ያልሆነ ምንም ነገር? ”

127 በምድር ሳለሁ እጅግ ጥሩ ሰው ነኚ ብየ አሰብ ነበር፡ በዚያ ግን ተኰነንሁ አለ። አለም፡- “አይ። አይ፡ የኔ ያልሆነን ነገር አንሰቻለሁ።”

“እንግዲያውሰ ፍጹም አልነበርክም፡” አለው። እሱም፡- “አዎን፡ ፍጹም አልነበርኩም፡” አለ።

128 ሲናገርም ርግቡ ካለበት ከታላቁ ብርሃን አሁን አሁን ይፈነዳል እያልኩ እጠባበቅ ነበር፤ “ተኰነነ!” ወድያው ግን ከኋላየ ድምጽ ሰማሁ፡ ይላል። በህይወቱ ከሰማው የእናት ድምጽ ይልቅ የጣፈጠ ድምጽ ነበር። ለማየትም ዞር አልኩ አለ። በፊቱም፡ በህይወት ዘመኑ ከአየው ከየትኛውም ፊት ይልቅ የሚራራ፡ ከትኛይቱ እናት ፊት ይልቅ የሚያኣኣ ፊት ቆሞ አየ። እንዲህም አለ ይላል፡- “አባት ሆይ፡ እውነት ነው ዳንኤል ከሪ ፍጹም አልነበረም፡ በምድር ግን ሰለ'ኔ ቆሟል፡ ሰለ'ኔ ጸንቷል። በምድር ሰለ'ኔ ቆሟል፡ ሰለዚህ አሁን በሰማያት እኔ ሰለ'ሱ እቆምለታለሁ። ሐጥያቱ ሁሉ ወደ መዝገቤ ውስጥ እውሰድለታለሁ።”

129 ወንድሜ፡ ዛሬ ከአንተ እንዲርቅ የምታሳዝነው ከሆንክ፡ በዚያች ቀን ማን ይቆምልሃል? ከዚህ በላይ መሰበክ አይቻለኚም፡ ራሶቻችን ዝቅ እናድርቅ።

130 የተወደድክ አምላክ፡ የሞትክልን ውድ ጠቦት፣ ቅን፣ ትሑት፣ የትሑታን ትሑት። ለወፎች ጎጆ፣ ለቀበሮዎች ጉድጓድ አላቸው፡ አንተ ግን፡ የክብር ጌታ ሆነህ ሳለህ፡ አንዲት ማረፍያ የሌለህ! አንተ ሰትወለድ፡ አንተን የሚያለብሱበት ልብሰ እንኳ አልነበራቸውም። አምላክ ሆይ፡ ታዲያ ልብሶቼ ምን ይፈይዱልኛል? በዚያች ቀን ምን መልካም ነገር ያደርጋል? መኪናየሰ ምን ትፈይድልኛለች? ቆንጆ ቤት ምን ይጠቅመኛል? ወዳጅ አልነበረህም፡

ጓደኛ ሊሆንህ የወደደ አልነበረም። አንተን ለማገዝ እጁን መዘርጋት የወደደ አልነበረም። በዚያ ቀን ግን "ተርቤ፡ አላበላችሁኝም፣ ታርዤም፡ አላለበሳችሁኝም።" እንደምትል ተናግረሃል። ታዲያ ጌታ ሆይ፡ ያለን ሁሉ በዚያች ቀን ምን ይጠቅመናል? ለአንተ የሚቆሙ አርገን፡ ምንም በማይሳነው፣ በሁሉም ሰፍራ በሚገኘው በህልውናው ፊት፣ የምንቀርብባት ያቺ ቀን በደረሰች ጊዜ... አምላክ ሆይ፡ በታላቁ ብርሃን መካከል ከተዘረጉት ክንፎቿ ጋር፡ ርግቧን በምንሰማበት ቀን፡ አንተ በብርሃንህ ውስጥ ሰታድር፡ ዘለአለምን ሁሉ ያበራል!

131 "ያለ ወንድም፣ ያለ ፓስተሬ፣ ያለ እናቴ፣ ብቻየን በራሴ መቆም ባለብኝ ጊዜ፡ አባቴ ሳይኖር፣ ሚስቴ ሳትኖር፣ ልጆቼ ሳይኖሩ፣ አምላክ ሆይ፡ ምን ይውጠናል፡ ጌታ ሆይ? ያኔ ምን ሊውጠኝ ነው? ምናልባት ዛሬ ጸሐይ ከመጥለቋ በፊት። ምን ማድረግ አለብኝ? ምን ላድርግ? ክርስቶስ ሆይ፤ ዛሬ ምርጫየ አደርግሃለሁ። አሁን ለአንተ እቆማለሁ! ስለ ሌሎች የማወራውን ሁሉ እተወዋለሁ። ቁጣየን ሁሉ እተዋለሁ። መለያየቶቼ ሁሉ እተዋቸዋለሁ። ሁሉንም እተዋለሁ። ጌታ ሆይ፡ ሸልተኝ፡ ያለኝን ሁሉ ውሰደው። ጌታ ሆይ፡ እኔን ውሰድ። በቦታህ—ላይ—መቆም እሻለሁ። መሸለት እፈልጋለሁ። ራስ ወዳድነት ሁሉ፣ ትዕቢት ሁሉ፣ ግድየለሽ ሁሉ፣ ነገር ሁሉ ከእኔ እንዲነሳ እፈልጋለሁ። ከዚያ'ማ እንደተሸለተ በግ፡ ለአንተ መቆም እወዳለሁ፤ የሕይወት ደስታ የሚሉት ደስታ ሁሉ ለመተው ፈቃደኛ ነኝ፤ ዳንሶች ሁሉ፣ ፓርቲዎች ሁሉ፣ የባለጌ ልብስ ሁሉ፣ ሜክ-አፕ፣ ሊፕስቲክ፣ የጥፍር ቀለም፣ እና ዓለምን የሚመስሉ ግድየለሽ ነገሮች ሁሉ። ደግሞም፡ 'ዓለምን አትምሰሉ። ከዓለም ጋር አትወዳጁ፡ ከመካከላቸው ውጡ!' ብለሀናል። አምላክ ሆይ፡ እርዳኝ ጌታየ። ሸልተኝ ዛሬ። እንደማይሰማ፣ አፉን እንደማይከፍት፣ ዝም ብሎ እንደሚሸለት እንጂ፣ እንደማይቃወም በግ ተቀበለኝ።"

132 አምላክ ሆይ፡ ምን ልዩነትስ ይፈጥራል! ሚስቴን፣ ልጄን፣ አባቴን፣ እና ወንድሜን ወሰደህ ያኔ ሰትሸልተኝ ትዝ ይለኛል። ጥርት አርገህ ሸልተኸኛል። በዚህ ሁሉ፡በልቤ ውስጥ፡ እንደምወድህ አውቃለሁ። አቤት የባረከኝ ብዛቱ! መልካምነትህ መብዛቱ! አሁን የሆንኩትን ሁሉ፣ መሆን የምችለው ሁሉ፣ ገና የምሆነውም ሁሉ፡ ጌታየ፡ ከአንተ ነው፡ አንተው ነህ። ጥፋቴን እናዘዛለሁ፣ ያደረግኩትን ኣና ያሰብኩትን ሁሉ ንሰሓ እገባለሁ። ጌታ ሆይ፡ በቃ ሸልተኝ፡ በግህ መሆን እሻላሁ።

133 ይሄ ብቻ አይደለም፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማለዳ እዚህ ያሉ ሰዎች ሁሉ ተቀበል፡ በግ ሁሉ፡ እና በግ ለመሆን የሚሹ ሁሉ፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማለዳ፡ ሁሉንም ሸልታቸው። ትንንሽ እግሮቻቸው በወንጌል እርሻ ላይ አቁማቸው። አሁን መንፈስ ቅዱስ ወደ ንሰሓ ይምራቸው፡ በእግዚአብሄር ነገሮች ላይ ግድየለሽ እንደነበሩ ይወቁ። ግድየለሽ ሁሉ፣ ዓለም ሁሉ፣ እና የዓለም የሆነውን ሁሉ፡ ይሸልትላቸው። ጌታ ሆይ፡ በፊትህ የተረጋጉ እና መልከ መልካም ሆነን እንጸና ዘንድ፡ ዛሬ ማለዳ ይህ ሁሉ ሸልተህ ዳግም-እንደተወለዱ ክርስትያኖች አርገን። ይሁንልን፡ ጌታየ።

134 እኔ እወድሃለሁ። የአየር ሁኔታው ሞቃት ቢሆን ባይሆን፣ ብወደውም ባልወደው፣ መሄድ እፈልጋለሁ። መቀጠል ፈልጋለሁ። በዚያ ቀን በእኔ ጉዳይ

ስለ'ኔ እንድትቆም ስለምፈልግህ፡ ለአንተ መቆም ፈልጋለሁ፡ "አዎን፡ ለእኔ ቆሟልና፡ እቆምለታለሁ፡" ትል ዘንድ። አምላክ ሆይ፡ ስጠን ዛሬ።

135 እያንዳንዱ ራስ እና ልብ ሁሉ፡ ዝቅ እንዳለ። በዚህ ማለዳ በራስ መንገድ መሄዱን የተገነዘበ ሰው ማየት እፈልጋለሁ፤ ማድረግ የሌለባችሁን ነገር አድርጋችሁ፣ በዚህ ማለዳ ግን ጌታ እንዲሸልትላችሁ የምትፈልጉ፡ እና፡ "ትክክለኛ በግ፡" ቢያደርገኝ የምትሉ ካላችሁ፡ እጆቻችሁ ከፍ አርጉልኝ። ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት። ጌታ ይባርክህ፡ ወንድሜ። ጌታ ይባርክህ፡ የኔ ወንድም። "ጌታ ሆይ፡ ቆሜአለሁና፡ ሸልተኝ። የሚል ሌላ ሰው ካለ። በግ ነኝ። ብቻ ዓለምን ከእኔ አሰውግድልኝ እንጂ፡ አፌን እንኳን አልከፍትም የሚል ሰው።" ጌታ ይባርክህ፡ ወንድም። ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት። ጌታ ይባርክህ፡ ታዳጊው ልጅ። ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት። ጌታ ይባርክሽ፡ እህቴ። "ሸልተኝ፡ ጌታ ሆይ።" እህት ገርቲ። አንቺም ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት። ጌታ ይባርክሽ፡ እህት። "አሁን ሸልተኝ፡ ጌታ ሆይ። ዛሬ ማለዳ ስለ አንተ እንድቆም ፈልጌአለሁና—ዓለማዊ ነገሮች ሁሉ... ዓለማዊ ነገሮች ሁሉ ከእኔ እንዲወገዱ እፈልጋለሁ። እንደተሸለተች በግ ሆኜ መቆም እፈልጋለሁ። እኔ የአንተ አንተም የእኔ እንድትሆን እፈልጋለሁ። እጄን ከፍ አድርጌልሃለሁና፡ ትቀበለኛለህ፡ ጌታየ? " ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት። ጌታ ይባርኮት፡ የተከበሩ። ጌታ ይባርካችሁ። ጌታ ይባርኮት፡ የተከበሩ። ጌታ ይባርኮት፡ የተከበሩ። ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት። ያንቺም አይቼዋለሁ፡ ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት። ተባረክ፡ ወንድሜ። ጌታ ይባርክሽ፡ ወጣት እመቤት። ጥሩ ነው። ከኋላ ያለሽው እናት፡ ጌታ ይባርክሽ። ጌታ ይባርክሽ፡ እህት። እውነት ነው፡ ቅኖች ብቻ ሁኑ። "እሱን የማይወክል በውስጤ የሚገኝ፡ የትኛውን ራስ ወዳድነት ከእኔ እንዲያስወግድ ጌታን እጠብቀዋለሁ፡ በእኔ የሚገኝ የትኛውም ግድየለሽነት። በዚህ ማለዳ፡ ፈጽሞ እንዲሸልተኝ እፈልጋለሁ። እንደሱ እንድሆን ፈልጌአለሁ። ስለ መብት ይሁኑ አይሁኑ አይገደኝም፤ መብቶች የሉኝም። አንድ መብት ብቻ አለኝ፡ እሱም፡ ወደሱ መምጣት ነው። ሌላው ራሱ ይጨነቅበታል።"

136 ክርስቶስን በንስሓ ተቀብሎ የማያውቅ ሐጥያተኛ ካለ፤ ያልዳናችሁ፤ በዚህ ማለዳ በጸሎት እንድናስባችሁ የምትፈልጉ ካላችሁ፤ እስኪ እጅህን ከፍ ታደርገው፤ ሐጥያተኛ ወዳጄ? እግዚአብሔር ይባርክህ። ሌላም ካለ እጆች ይነሱና፡- "ለእኔ ጸልይልኝ፡ ወንድም ብራንሃም። ክርስትያን አይደለሁም፡ ከእግዚአብሄር ጋር መቼ እንደምገናኝም አላውቅም። በመዝጊያው ላይ፡ አሁን በጸሎት ቃል ላይ እንድታስበኝ—እፈልጋለሁ፡" የምትሉ ካላችሁ። እሺ እኔ እንድጸልይላችሁ፤ እጆቻችሁ ከፍ ታደርጉልኛላችሁ? እሱ ያያል። ጌታ ይባርክሽ፡ ወጣት እመቤት። ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት። ጌታ ይባርኮት፡ የተከበሩ። ሌላ ካለ፡- "ይህ ነገር... እፈልጋለሁ፡ እፈልገዋለሁ የሚል"

137 እስኪ ወደ ዓለም የተመለሳችሁ ሰንቶች አላችሁ? "ኡህ" ፣ "ወንድም ብራንሃም፡ ለዚህ እንኳ አልታዘዝም፡" ትላላችሁ። ግን፡ ተመልከቱ፡ የርህራሄው ርግብ ከእናንተ ዘንድ ከተለየ፡ ወንድሜ፡ የሆነ ችግር አለ። አንዳቹ ለሌላው መሸካከም ከተሳናችሁ የሆነ ችግር አለ። ሰውን ሁሉ ከውስጥ ከልባችሁ ይቅር ማለት ሲሳናችሁ፤ ምንም ዓይነት በደል ቢበድሏችሁ ወይም ምንም ይበሏችሁ፡ ከልባችሁ ይቅር ማለት ካልቻላችሁ፤ ኢየሱስ ሲናገር፡- "ለሰው ሁሉ መተላለፋቸውን ይቅር ካላላችሁ፤ ከልባችሁ ካላላችሁ፡ የሰማይ አባታችሁም ይቅር አይላችሁም።"

138 እስኪ አሁን፡ በዚህ ሞቃታማ የአየር ሁኔታ፡ እስኪ ጌታ ዛሬ ቢጠራችሁስ? በተዘጋጀች ቤተክርስትያን ውስጥ፡ የሚፈስ ምንጭ በተከፈተበት፤ መንፈስ ቅዱስም በህንጻው ጣራ ስር ሆኖ፡ እናንተን ጨዋዎች እና ሰላማዊ ለማድረግ ወደ ልባችሁ ለመመለስ እና ለመግባት ተዘጋጅቷል። "ምን ላድርግ፡ ወንድም ብራንሃም? " በግ ብቻ ሁኑ። እናንተ በግ ስትሆኑ መንፈስ ቅዱስ ወድያው ይመጣል። በራሳችሁ መንገድ ለመሄድ፡ የተሳሳተ መነሻ፤ የተሳሳተ—የተዛባ ሐሳብ ይዛችሁ፣ ለመተው ፈቃደኞች ካልሆናችሁ ግን፤ መንፈስ ቅዱስ በፍጹም አይመጣም።

139 ራሶቻችን ዝቅ እንዳደረግን፡ እጆቻችሁ ካነሳችሁ ሰዎች መካከል… ኢየሱስ፦ "ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ህይወት አለው እንጂ፡ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም ብሏል።" ዮሃንስ፡ 5፥24። አሁን ግን ወደ መሰውያው መጥታችሁ፡ እዚህ መምበርከክ ከፈለጋችሁ፡ ከዚህ በፊት ከእናንተ ጋር የነበረ፣ ወይም አሁን እንዲኖራችሁ የምትፈልጉት፡ ጨዋ እና ሰላማዊ ሰሜት፡ ዳግም ወደ እናንተ እስኪመለስ ድረስ አብረን እንጸልይ። ራሶቻችን ዝቅ እንዳደረግን፡ **በደም የተሞላ ምንጭ አለ፡** እያልን እየዘመርን፤ በርከክ ብላችሁ ለመጸለይ፡ እንድትመጡ እፈልጋለሁ። መምጣት የሚፈልግ ሁሉ፡ መድረኩ ጋር ለተወሰነ ጊዜ በርከክ በሉና አልቅሱ ጸልዩ።

በደም የተሞላ የደም ፏፏቴ አለ፤
ከአማኑኤል ደም ስር የተቀዳ፡
ሐጥአን ከሰሩ ወድቀው…

ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት፡ ነይና በርከክ በይ።

ይፈታሉ…

140 ልቦቻችሁ ጋር፤ ራሶቻችሁ ዝቅ እንዳደረጋችሁ ተሰፋ አደርጋለሁ። ዛሬ ማለዳ ይህን እጥር በሰበረችው ሴት ምክንያት፤ በራሳችሁ ልታፍሩ እንደሚገባችሁ ታውቃላችሁ? እግሮቿ ያባበጡባት፣ ምስኪን፣ የሸበተች፣ ጥቁር ሴት፣ ወደ መሰውያው መጥታለችና።

141 ያኔ ድሮ፡ በባርያ ንግድ ጊዜ፡ አንድ ጥቁር ሽማግሌ መዳን ሆነለት። ልክ እንደዳነ፤ ወደ አለቃው ሄዶ፤ እኔ ነጻ ነኝ አለው። እሱም፦ "ምን ነኝ? " አለው።

"ነጻ ነኝ፡" አለው። ከዛ በኋላ ነጻ አደረገው።

142 እነሆ በዚህ ማለዳም ለመዳን የመጡ ሌሎች ብዱኖች አሉ። (እሱ ነጻ ነኝ ብሏል።) ሰው ሁሉ ይጸልይ፤ ከቻላችሁ በሀይል ጸልዩ፡ መንፈስ ቅዱስ ዛሬ በሚወስኑ ሰዎች ላይ ስራውን እየሰራ ነው።

እሱም አለው፦ "ነጻ ነኝ ነው ያልከው፡ ሞስ? " እሱም፦ "አዎን፡ ጌታዬ፡ አለቃ። ነጻ ነኝ።"

143 "ነጻ ከሆንክ፡ በል እኔም፡ ነጻ አደርግሃለሁ። ሂድና ወንጌል ሰበክ፡" አለው።

144 በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ፡ ብዙ ነጭ ወዳጆቹ ሊያዩት መጡ፡ በመጡ ጊዜ፡ ኮማ ውስጥ የገባ ይመስለኛልና፡ እንዲህ አለ። ሲነቃ፦ "የሞትኩ መስሎኝ

ነበር፡" አላቸው። (ጌታ ይባርክህ ወንድሜ፡ በቃ፡ እዚያው ጋር በርከክ በል።) "የሄድኩ መሰሎኝ ነበር።" አላቸው።

"ምን ምን አየህ፡ ሞስ? " አሉት።

145 "በሩጋ ጠጋ ባልኩ ጊዜ፡ አየሁት።" አላቸው። "እሱን እያየሁ፡ ቆምኩኝ።" አላቸው። ከዛ በኋላ፡ "አንድ መልአክ መጣና፡ 'ሞስ ወዲህ ና፡ አለኝ። ለብዙ ዓመታት ወንጌልን ስብከህልና፡ መጎናጸፊያ እና አክሊል ተዘጋጅቶልሃል።'" እሱም እ፦ '"ስለ መጎናጸፊያ እና አክሊል አትንገረኝ። መጎናጸፊያ እና አክሊል አልፈለግኩም። ፍላጎቴ እሱን ማየት ነው አለው።'" የሁሉም ክርስትያን ባህርይ ይሄ ይመስለኛል።

146 እዚህ በቺካጎ ነውና፡ ትንሽ ቆየት ብሏል፤ ኮሊሰየም ላይ ገብቼ፤ ማለቴ፡ ሙዝየም ውስጥ ገብቼ፡ እዚያ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ተመለከትኩ። በራሱ ጸጉር ላይ ክብ መላጣ ያለው፡ ጥቁር ሽማግሌ አየሁ። ኮፍያው እጁ ላይ ይዞ፡ ወድያ ወዲህ ይላል። አየሁት። እነሰ ያለች ቦታ ላይ አየት አደረገና፡ ዘሎ መለሰ አለ፡ ወድያውም ባረጀው ጥቁር ጉንጩ ላይ እንባ ይፈስ ጀመር። መጸለይም ጀመረ። ለጥቂት ጊዜ አየሁት። እንደገና አየት አድርጎ፡ አሁንም ማልቀስ ጀመረ። ጠጋ አልኩትና፡ "አለቃ፡" አልኩት።

እሱም፦ "አቤት፡ ነጭ ወዳጄ? " አለኝ።

አልኩት፦ "እኔ እያየሁህ... ስሜታዊ ያደረገህ ምንድነው? ለምንድነው እጅግ ስሜታዊ የሆንከው? "

147 አለኝም፦ "በሆነ ወቅት ላይ ባርያ ነበርኩ።" "ጌታየ፡ ጎኔን ብትዳሰሰው፡ ጎኔ ላይ ጠባሳዎች አሉ" አለኝ። "በዚህ በመስታወት ጎጆ ውስጥ፡ ያለው ይህ ልብስ።" አለኝ።

"ልብስ እንደሆነ ይታየኛል፡ ግን ምን የተለየ ነገር አለው? " አልኩት።

148 አለኝም፦ "ላዩ ላይ ያለው ቀለም፡" ፣ "የአብራሃም ሊንከን ደም ነው፡" አለኝ። "የባርነት ሰንሰለት ከእኔ ላይ የበጠሰ ደም ይህ ነው።" አለኝ። "ታዲያ፡ አንተ ነጭ ሰው፤ አንተንስ፡ ስሜታዊ አያደርግህምን? " አለኝ።

149 አንገቱ ላይ እጆቼን ጣል አደረግኩና፦ "ጌታ ይባርክህ፡ ወንድሜ። ስሜታዊ የሚያደርገኝ ሌላ ደም አለኝ።" አልኩት።

"አገልጋይ፡ እሱ ደምም፡ አውቀዋለሁ።" አለኝ።

150 "የባርነት ሰንሰለት ወሰዶልኛል።" አልኩት። እሁድ ወጥቼ መሮጥ ማውደልደል፣ መጥፎ ቀልድ የሚቀልድ ሰው ነበርኩ። ጌታ ሆይ፡ እንደው፡ እንዴት እንዴት ፈጸምኩት? ይሄን የፈጸምኩበት ጠባሳዎች አሁንምም ልቤ ውስጥ አሉ። ማስርያውን ከእኔ ሰላወለቀ ግን ደስ ይለኛል። ሰለኔ ቆሟልና፡ ሁሉ ጠፍቶልኛል አሁን።

151 የሆነ ቀን ላይ፡ አንዲት ጋጠወጥ ሴት አይቼ፡ ልገሰጻት ስፈልግ። እግዚአብሄር ራእይ አሳየኝ። የእኔ ሐጥያት እንደሷ ሐጥያቶች ታላቅ መሆናቸውን አሳይቶኝ፡ ወድያውኑ ጸለይኩላት። አገልጋይ መሆኔን ነግሬአት፡ ቀረብ ብየ በሷ ጎን ቁጭ አልኩኝና እንድታፍር አደረግኳት። ሁለቱ ወንዶች ጓደኞቿም... ስድሳ-አምስት ይሁን ሰባ ዓመቷ ናት፡ ሁለቱ ጓደኞቿም ጭምር ተንበርክከው ሁሉም ልባቸውን ለክርስቶስ ሰጡት። ኦህ፡ ማይ፡ አቤት ልዩነት!

152 እናንተ'ሳ? በዚህ ማለዳ፡ ብዙ ሐጥያት ሰርታችኋል ወይ፡ መንፈስ ቅዱስ ለመንካት እስኪጸየፍ ድረስ ልባችሁ ጠቁሮ ተበላሽቶባችኋል? ምናልባት ርግቧ ለዘላለም በርራ ይሆን፡ ላትመለስ ሄዳለች።

153 ጌታ ይባርክሽ፡ የኔ ማር። ታዳጊዋ ልጅ እየመጣች ናት። ጌታ ይባርክሽ፡ የኔ ጣፋጭ። "እቺ ህጻን ልጅ ምን ታውቃለች፡" ካላችሁ፤ ኦህ፡ አዎን፡ ታውቃለች። ሌሎቻችሁ እንዳነበባችሁት የፍቅር ታሪኮች እና ጋዜጣዎችን አላነበበችም ይሆናል። ነገሩ እንዲህ ነው፤ ልቧ ስስ ልብ ነው። ኢየሱስም፦ "ህጻናት ወደ'ኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው፡" ብሏል።

154 መምጣት የሚፈል ሌላ ሰው አለ፡ በማለዳው ሊቀላቀል የሚወድ ካለ? መሰውያው ክፍት ነው። በቃ ሌላው ነገር፡ አንዴ ድግመን እየዘመርን፡ እነዚህ ሐጥያተኞች የንሰሓ ጸሎት እየጸለዩ እኛ ጸሎት እናደርጋለን።

ሌባው በሞት አፍ በደስታ
ምንጩን ሲያይ... (አዎን፡ ነገሩ ሁሉ ተወሰዶበት፡ ምስኪኑ
  ሰው አልቆለት ነበር።)
እኔም ብሆን፡ ከንቱ እንደሱ...

155 አትመጡም አሁን? እናንተ ከዚህ የተሻለ ይምታውቁ፡ አትመጡም ወይ? መጽሀፍ ሲናገር፦ "በጎ ለማድረግ አውቃችሁ፡ ለማታደርጉት፡ ከሐጥያት በላይ ነው።" አትወጡምን? ጥፋተኛ መሆናችሁ ታውቃላችሁ። መንገዳችሁን ወዲህ አቅኑና በመሰውያው ስር ተንበርክካችሁ፡ ስለበደላችሁት በደል ጌታን ይቅርታ ጠይቁ። መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ዳግም የዋሆች፣ ጨዋዎች፣ እና የተረጋጉ ያድርጋችሁ። አትመጡም? አስታውሱ፡ እሱ ለእናንተ ሄዶ፡ እናንተ ግን ብትሞቱ፡ የሚጣበቅላችሁ አታገኙም። ዛሬ ማለዳ ስለሱ እንድትቆሙ ይፈልጋችኋል። ጌታ ይባርክህ፡ ወንድሜ።

156 እጠብቃለሁ። በቃ ይሄው ነው፡ ከዚህ ቤተክርስትያን ኩነኔ የተሰማቸው ሰዎች አስራ አምስት ሰው ብቻ ናቸው? ሰላም፣ ትሕትና፣ ጨዋነት፣ እርጋታ የሞላበት ህይወት ኖራችኋል? አሁን ይህ ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ ምሪት ነው። ይቅር ብላችኋል፣ ጠላቶች የሉአችሁም? ያለፈ ኑሮ፡ ከሐጥአን ኩነኔ በላይ? እንደ አሕዛብ ኑሮ አትኖሩም፡ የተለየ ኑሮ ትኖራላችሁ? ሕይወታችሁ የተለየ አቅጣጫ ይዟል? የተረጋጋው ቅዱሱን መንፈስ በልብህ ዙፋን ላይ ተቀምጦ፡ በሰላም በእርጋታ እና በፍቅር ከሰዎች ጋር፤ እንድትኖር ያደርግሃል? አንተ ጨዋ መሆንህን፣ ጎረቤቶችህ ሁሉ ያውቃሉ፣ ወዳጆችህ ሁሉ ያውቃሉ፣ የተረጋጋ፣ ቅን፣ ትሁት ክርስትያን እንደሆንክ? የእግዚአብሄር ርግብ ከአንተ ጋር እንደሆነች? እርግጠኛ ነህ? ምናልባት ይሄ የመጨረሻ እድልህ ሊሆን ይችላል። ጥሩ እንግዲህ።

157 ለእናንተ በመሰውያው ፊት ላላችሁ፡ ጌታ ይባርካችሁ። መንፈስ ቅዱስ ፍርድን ወደ እናንተ አቅርቧልና። አሁን አይፈረድባችሁም። መብታችሁን ተጠቅማችሁ፡ "ኦህ፡ የቆየ ክርስትያን'ኮ ነኝ። እዚያ መውጣት አይገባኝም" ለማለት አልሞከራችሁም። መሰውያው መጀመርያ ቀናችሁ የሆነ፡ ጥቂቶቻችሁ፦ "መብቴ ነው፡ ብፈልግ ሀጥያተኛ ሆኜ መቀጠል እችላለሁ።" አዎን፡ ልክ ነው። ነጻ የሞራል ምርጫ አላችሁ፡ ያሻችሁን ማድረግ ትችላላችሁ። ዛሬ ጠዋት ግን መብቶቻችሁን ንቃችኋል። "ምን ይሉኛ ይሆን፤ ወደ መሰውያው ሄጄ ክርስትናን

መቀበሌ፡ ሰዎች ምን ይሉኛ ይሆን? ” ትላላችሁ። እግዚአብሄርስ ምን ይላል? እንድትመጡ ተናገራችሁ፡ እናንተም ታዛችኋል። አሁን መብታችሁን ጥላችኋል፡ ዛሬ በልባችሁ ሰፍራ እንዲኖረው መንፈስ ቅዱስ ለመቀበል መጥታችኋል። እንዲያደርግ አውቃለሁ። አውቀዋለሁ ያደርገዋል። እንደሚፈጽመው ቃል ገብቷል። እንደው፡ ማንም አይገድበውም፡ ከመምጣት የሚያግደው የለም። እሱ ግን ወደ እናንተ ለመግባት እየተተባበቀ፣ ሰፍራን ፍለጋ፡ ይለምናል፣ ይጮኻል፣ ሞቷል፣ ሌላም ሁሉ አድርጓል።

158 እናንተም በመሞቻ ሰዓታችሁ፡ የሞት መልአክ መጥቶ በአልጋው ግርጌ ሲቀመጥ፡ አንድ ቀን እሺ አለማለታችሁን አውቃችሁ፡ እጅግ አስከክፊ የሆኑ ነገሮችን እየተመለከታችሁ፡ ምንም ያህል፡ ምንም ያህል አብዝታችሁ ብታለቅሱ፡ ነፍሳችሁ ይጠቁራል፣ ይጨላልማል። ኤሳው በጸጋው ላይ… ማለት፡ በጸጋው ቀን ላይ ሐጢያት ሰራ፤ ዳግምም ዕድል አላገኘም። ስሕተቱን ለማረም ሰፍራ ፈልጎ፡ አምርሮ አለቀሰ፡ ነገር ግን አልተገኘለትም። እግዚአብሄር ግን አስቀድሞ ጠርቶት ነበር።

159 እናንተ ግን ዛሬ ጠዋት ወደዚህ ለመምጣት መብታችሁ ሁሉ እና ወዳጆቻችሁ ሁሉ፣ ሌላም ሁሉ፡ ስሜታችሁን ሁሉ፡ ጥላችኋል። ተንበርክካችሁ ከእግዚአብሄር ጋር ለመነጋገር፡ መብቶቻችሁን ሁሉ ክዳችኋል። እኔ ግን ክርስቶስ፦ “ወደ እኔ የሚመጣውን፡ ፈጽሜ ወደ ውጭ አላወጣውም።” ብሎ እንደተናገረ፡ በጌታ ቃል እነግራችኋለሁ። አሁንም ገና በመሰውያው ስር እንደሆናችሁ፡ ንስሃ ግቡ፡ ስላደረጋችሁት ነገር ይቅርታን ጠይቁት።

160 ሰዎች ሲተመቁ መንፈስ ቅዱስ የማይቀበሉበት ምክንያት ይሄው ነው፡ እግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጣቸው ይፈልጋል። ከልባቸው ግን ንስሐ አይገቡም። እሱ ትሑት፣ ጨዋ፣ እና የተረጋጋ እንድትሆኑ ይፈልጋል። በልባችሁ ራስ ወዳድ ሆናችሁ የምትነሱበት ምክንያትም ይህ ነው። ኦህ፡ ምናልባት ስትነሱ፣ ትጮኹ ይሆናል፣ በልሳን ትናገራላችሁ፣ ወይም ሌላ፤ ይህ ግን መንፈስ ቅዱስ እንድትቀበሉ አያደርግም። ከዚያ ስትነሱ የተለየ ሰው መሆን አለባችሁ። ከዚያ ስትነሱ፡ የእግዚአብሄር መንፈስ ያረፈበት ጨዋ፣ የተረጋጋ፣ ገር፣ ትሑት መሆን አለባችሁ። በቀጣይ ዓመት፡ ፈተናውን ሁሉ እዩትና ምን ያህል እንዳለፋችሁ አስተውሉ፡ ዳርቻችሁን በየቀኑ እየሰፋ እንደሆነ እዩ። ያም ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ታጋሽነት፣ ገርነት፣ ጨዋነት፣ ትዕግስት፣ እምነት ነው። አሁን፡ ንስሃ ግቡና እንደምትፈልጉት ጌታን ንገሩት። እሱ… ያደርገዋል።

161 ማርየ፡ እዚያ ያለሺው፡ ብላቴና፡ እናትሽ አብራሽ ቆማ እጆቿን የጣለችብሽ። ተባረኪ። አንቺም እንደነሱ አርጊ።

162 ይህች የተወደደች ጥቁር ሴት፡ በመሰውያው ላይ ተደፍታለች። ምናልባት ምግብሽ የበቆሎ ቂጣ ወይም በቆሎ ቦጅቦጅ ሊሆን ይችላል፡ ጠባብ መንገድ ላይም ትኖሪ ይሆናል፡ እኔ አላውቅም፡ እህቴ። ዛሬ ጠዋት ግን በሰማያት ቤት ተዘጋጅቶልሻል፤ ጌታ ልብሽን ይባርከው። አዎን።

163 እሰኪ ወደ መሰውያው ተመልከቱና፡ የሸበተች እመቤት እና፡ አንገቷን የደፋች ወጣት ሴት እዩ፤ ጨርሳ-ነጭ-ጸጉር ያበቀለች እናት። ጌታ ሆይ! እዩ ሰዎች ተንበርክከዋል፡ የተለያዩ ሰዎች። ንስሐ ግቡና፡ ይቅርታ ጠይቁት።

ሁለተኛ አይለመደኛም በሉት። ከዛሬ ጀምሮ፡ ልዩነቶቻችሁን ሁሉ፡ በጸጋው ያበቃለታል። ጨዋዎች እና የተረጋጉ ሁኑ። እሱ ወደሚመራችሁ ለመሄድ ትሁታን ልትሆኑ ይገባል።

164 ሰዎች የሚሏችሁ ሁሉ፡ ምንም ያህል እውነት ቢመስልም፡ ባለንጀራችሁን ላለማማት መብቶቻችሁን በመተው። የምታወሩት ሁሉ፡ ስለ ኢየሱስ ብቻ ትናገራላችሁ። ትክክለኛ የሆነውን ነገር ብቻ ታደርጋላችሁ። ነፍስ ለማጥፋት አትወጡም። ንጹሁን ለማጥቃት አትወጡም። ነገር ግን ጀግኖች እና ቆራጥ ክርስትያኖችን አይታቿቸዋል፡ እንደነሱ ትሆናላችሁ። ክርስትያን ከሆናችሁ፡ ክርስትያን ነኝ ብላችሁ መናገር አይጠበቅባችሁም። ባነጋገራችሁ አይተው ያውቋችኋል። በውስጥም በውጭም ታትማችኋል።

165 አሁን፡ ልባችሁ ዝቅ እንዳደረጋችሁ፡ ንስሓ ግቡ። እግዚአብሄርን፡ "ይቅርታ" ጠይቁት፡ በሄድኩበት መንገድ "በራሴ አፍሬአለሁ፣" "ሁለተኛ እንዲህ አላደርግም፡" በሉት። እኔም ስለ እናንተ እጸልያለሁ። ወድያውም፡ ሰላም በልባችሁ ውስጥ እንደሚያድር፡ አምናለሁ፣ እንደሚፈስ ወንዝ ሰላው ወደ ነፍሳችሁ ይመጣል። ላትጮሁ ትችላላችሁ፣ በልሳን ላትናገሩ ትችላላችሁ፣ ላይ ታች ላትዘሉ ትችላላችሁ፤ ይሁን እንጂ አንዳች ነገር በልባችሁ ገብቶ ከመሰውያው ትሄዳላችሁ። በህትወት እስካላችሁ ድረስ ከጥንቱ የመከራ መስቀል ጋር መልህቅ የሚሆናችሁ ነገር። አሁን እኔ እንደምጸልየው፡ ጸልዩ። ተናዘዙ።

166 የሰማይ አባታችን ሆይ።ይህ ሞቃት፡ የላብ ሳጥን በሆነው፡ በዚህ በሚያልብ ማለዳ፣ የማንጠቅም ፍጥረት ስንሆን፡ አንተ ግን፡ አምላክ ሆይ፡ ከእኛ አልበህ አውጥተህልናል። መንፈሰ ቅዱስ ወርዶ፡ ሰዎች ስህተታቸውን እንዲያምኑ አርጓል። ሐጥያኃጢአት ይሠሩ ነበር። መንፈሳቸው እብሪተኛ ነበር። ጠበኛ፣ ነውጠኛ፣ ሁሉም-እናውቃለን-ባዮች፣ ንስሐ ለመግባት ግን የማይወዱ ነበሩ፣ የበደሏቸውን ሰዎች ይቅር ለማለት ፈቃደኛ አልነበሩም። ፈቃደኛ አልነበሩም፣ ዛሬ ግን መንፈሰ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል ወስዶ፡ በጨዋ ልባቸው ውስጥ አኖረው፤ እንዲህም አላቸው፦ "ያኔ ለመጀመርያ ጊዜ ወደ መሰውያው ስትመጡ ወደነበራችሁበት ሁኔታ መመልስ ትፈልጋላችሁ፡ ሰውን ሁሉ፡ ሰውን ሁሉ ወደ ምትወዱበት፡ እኔንም በማይሞት ፍቅር ወደምትወዱበት፡ መመለስ ትፈልጋላችሁ? እንግዲያውስ ተነሱና ወደ መሰውያው ቅረቡ።" እሺ ብሏል፡ ጌታ ሆይ።

167 ጌታ ሆይ፡ አሁን፡ ሐሳቦቻቸውን ትቀድሰው ዘንድ እጸልያለሁ፡ ልባቸውን ቀድሳት፣ ጨዋ እና ሰላማዊ አድርጋቸው። በመሰውያው ንስሐ ከገቡ በኋላ ሕይወታቸውን ለአንተ አሳልፈው ሰጥተው፡ ወደ ቤታቸው ይመለሱ። ምንም ነገር ቢፈጸም፣ ባል ቢቆጣ፣ ወይም ሚሰት ብትናደድ፣ ወይም ወዳጅ ቢቆጣ፣ ወዳጅ ሊሆን ይችላል ወይም የስራ ባልደረባ፡ "እኔ እንደ እርግብ ጨዋ እሆናለሁ።"

168 ደግሞም፡ በቀል የአንተ ነው፣ "እበቀላለሁ፡ ይላል እግዚአብሔር።" ጌታ ሆይ፡ ትክክል መሆኑን አረጋግጠናል። ጽና ብቻ፣ የዋህ ሁን፣ እግዚአብሔር ወደ በጉ ሲወርድ... ሲመጣ ታያለህ። ትክክል፡ በርግጠኝነት። መልካም እረኛ ህይወቱ ስለ በጎቹ ይሰጣል፡ ይመጣላቸዋል። ደግሞም ይመራቸዋል። ወዮለት

እጁን ለሚያነሳባቸው! ወዮለት አንዲት ክፉ ቃል ለምሚናገራቸው! “የወፍጮ ድንጋይ አንገቱ ላይ ታስሮ፡ ወደ ባሕር ልብ ቢወረወር ይሻለው ነበር። ብሏል፡ መላእክቶቻቸው ዘወትር የአባቴን ፊት ያያሉና።” አያችሁ? አምላክ ሆይ፡ ያስፈልገናልና... “ለነሱ ያረግከው፡ ለእኔም አርግልኝ።”

169 ስለዚህ፡ ጌታ ሆይ፡ እኔም፡ ጨዋ መሆን እሻለሁ። በዚህ ማለዳ፡ ራሴን በመሰውያው ጥላለሁ፤ ለዚህ ማለዳ ብቻ ሳይሆን፡ ዘወትር ማለዳ እና በየቀኑ። እንደ ኢየሱስ የተረጋጋሁ እና ጨዋ መሆን እሻለሁ። ይሁን፡ አባት ሆይ። አእምሮን የሚያልፍ የፍቅር ጥልቀት በነፍሳችን ላይ አፍስስ፡ መሆን እንድችል እርዳን አሁን።

ሰላም! ሰላም! ድንቅ ሰላም፡
(አሁን በልባችሁ ውስጥ አይሰማችሁም? ) ከላይ ከአብ ዘንድ የሚገኝ፡
... (ሃሌሉያ ሃሌሉያ)... መንፈሴ ላይ ይፍሰስ፡ ለዘላለም
ሰላም! ሰላም! ድንቅ ሰላም፡

170 እህት ጌርት ፒያኖው መሰውያዋ እርጋው ነው እንጂ፡ እሷም፡ መኰነኗ ለቤተክርስትያን ተናግራለች። መሰውያዋ፡ መሰዋውያዋ ፒያኖው እስከሆነ ድረስ፡ ባለችበት እንባዋ መንጽሮቿ አልፎ እየፈሰሰ፡ “እንዲጸለይልኝ፡ ለቤተክርስትያን ንገሩልኝ፡” ብላለች። ጌታ ሆይ! እኔም፡ መጽሓፍ ቅዱሴን አርሼ፡ንስሃ እገባለሁ። መሰውያየ ፑልፒቱ ነው።

ሰላም! (የእግዚአብሄር ሰላም።)
ከላይ ከአብ ዘንድ የሚገኝ፡ (ኦህ፡ ሃሌሉያ!)
... መንፈሴ ላይ ይፍሰስ ለዘላለም...

171 አምላኬ፡ ማንንም በድየ እንደሆነ፣ ወይም አንተን፣ ጌታ ሆይ፡ አንሳልኝ። የትንሿ ቤተክርስትያኔ፡ ሐጥያቷ ዛሬ ማለዳ ይነሳ።

172 እግዚአብሄር ይቅር እንዳላችሁ የርግቧ ሰላምም ዳግም በልባችሁ እንደገባ የተሰማችሁ ስንቶች አላችሁ? ሰፍራዋን ለመያዝ፡ አሁን በርራ ተመልሳለች። መንፈስ ቅዱስም ተመልሷል “ልጄ፡ ሁሌ አንተን ለማፍቀር ሰናፍቅ ኑሬአለሁ፡ ብሏል። አንተ ግን ከለከልከኝ። ባረጀው ራሰወዳድ መንፈስህ ማረፍ አልችልምና። አሁን ግን ስለተማረክልኝ፤ ዛሬ ማለዳ ወደ ልብህ ተመልሼአለሁ።” ስንቶቻችሁ ይህ ስሜት ተሰምቶአችኋል? እጆቻችሁ ከፍ አርጉት። እጆቻችሁ ከፍ አርጉት፡ አዎን፡ መሰውያው ሙሉ። ኦህ፡ ጥሩ ነው። ከጉባኤው ሰሜቱን የተሰማችሁ ስንቶች ናችሁ? እጆቻችሁ ከፍ አርጉ። (**ኢየሱስን መምሰል።**)

173 የሰማይ አባታችን፣ ስለ እንዲህ ዓይነቱ ምቹና፡ ቅዱስ ጊዜ እናመሰግናለን፡ ፖም በእጅ ወሰደን፡ ልም እስኪሆን ድረስ፡ ጨቅላ ልጅ አርፎ ሊመገበው እንደሚችል አርገን ፈጭተን፣ እንደምናሸው። ጌታ ሆይ፡ ልባችን እንዲሁ እንዲሆን እንፈልገዋለን። በሚሰማር-በተመታው፡ በተቀተቀጠ እጅህ ውሰደውና፡ እንዲህ በል፦ “እንደጎዳኸኝ አይተሃል፡ ልጄ? ከእጇታው ስትሸሽ ስትጎዳኝ ኖረሃል። ጎድተኸኛል፤ ኦህ፡ ልጄ ሆይ፡ **እንዲህ-እና-እንዲያ** ስታደርግ፡ ልቤ ስለአንተ ደምቷል። አሁን ግን ልብህን በእጄ ውስጥ ስለገባች፡ ትሁት እንድትሆን እሰራታለሁ። እንድኖርባት እና እንድጠቀምባት እሰራታለሁ። ዛሬ

ማለዳ በርሬ መመለስ እፈልጋለሁ፤ መኖርያየን በአንተ አደርገው ዘንድ፡ በርሬ መጥቼ አርፋለሁ።” ይሁን፡ አምላክ ሆይ። እንወድሃለን። ስለ ክብርህ፡ ይሁን። በኢየሱስ ሰም ጸለይን።

እንደ ኢየሱስ ለመሆን፡ ለ...

እንዲህ ማምለክ አትፈልጉም? ኦህ፡ ነፍሴ ተጥለቅልቃለች።

እኔ ከምድር...

በሚያመልኩት—ላይ እንዲህ ሲወርድ ስታዩት፣ ልባችሁ ጨዋነት አይሰማችሁም? የኔ ልብ′ማ በፍጥነት እየመታ ነው።

... ጉዞ ከምድር ወደ ክብር
እንደ እሱ ለመሆን ብቻ እጠይቃለሁ።

እስኪ እጆቻችን ወደ ላይ አርገን እንዘምር?

እንደ ኢየሱስ ለመሆን፡ ለ...

ውንድም ጆ፡ ወደዚህ ና ዛሬ ማለዳ አንተ አትጸልይም? ጌታ ይባርክህ። እስኪ በመሰውያው ቦታ ፈልግ፡ ወንድም ጆ። ጌታ ይባርክህ... ? ...

... ጉዞ ከምድር ወደ ክብር
ልመናየ እሱን መምሰል ብቻ ነው።

174 ሙቀት እንዳለ አውቃለሁ፡ ወዳጆች። አውቄአለሁ። ግን እንደኔ አይነት ስሜት እንደተሰማችሁ—ተሰፋ አደርጋለሁ። ኦህ፡ እኔ′ማ ብረር ብረር እያለኝ ነው። እንዴት ያለ አፍቃሪ ነው! ጌታ ሆይ! ምን ላድርግ? የት ልሂድ? የት እየሄድኩ ነው? ወዴት እያመራሁ ነኝ? ምን ሊሆን—ምን ሊሆን ነው? የዛሬ መቶ ዓመት የት እሆን ይሆን? ባላገኘውስ? የት አለ፡ ሌላ ጥላ የት አለ?

ከቤተልሔም ግርግም እንግዳ ወጣ፡
በምድር ላይ እንደ እርሱ ለመሆን እመኛለሁ ፤
በሕይወት ጉዞ ሁሉ ከምድር ወደ ክብር
ልመናየ እሱን መምሰል ብቻ ነው።

አሁን ሁሉም አንድ ላይ።

እንደ ኢየሱስ ለመሆን... (ሰብሐት ለእግዚአብሔር! አዎን፡ ጌታ! አዎን ጌታ! እንደ ዓለም ሳይሆን ፤ እንደ አንተ!)
... እሱን ለመምሰል;
በሕይወት ጉዞ ሁሉ ከምድር ወደ ክብር
አንዲት ብቻ እጠይቃለሁ... ? ...

175 አንገታችሁን ዝቅ እንዳለ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ። መንፈስ ቅዱስን እያሳዘነ ያለ ሰው አለ። ጥሪ የቀረበለት ሰው ነበር። እንደሱ ነብዩ፡ በጌታ ኢየሱስ ሰም እናገራለሁ። ልቡ ሲቆሰል እየዋለሁ። መውጣት እያለበት፡ አልታዘዘ ያለው ሰው፡ በዚህ አለ። አሁን አትወጣም?

በሕይወት ጉዞ ሁሉ ከ...

አዎን፡ እህት፡ ግን ከአንቺ ሌላ አለ።

… ክብር
ልመናየ እሱን መምሰል ብቻ ነው።

ኢየሱስን ብቻ መምሰል… (ፍላጎቴ ሁሉ፡ እንደ'ሱ፡ ትሁት መሆን፡ ትሁት እና ዝቅ ማለት ነው።)
እኔ በምድር ላይ…

አሁን አትነሱም? እግዚአብሔር ስትንቀሳቀሱ ማየት ይፈልጋል፣ ብዙዎቻችሁ አላችሁ።

ሁሉ በአንዴ…

176 እንደምትመጡ አውቅ ነበር። ጌታ ይባርካችሁ። ጌታ ይባርካችሁ። ጌታ ይባርካችሁ። ይህው ነው። ይህው ነው። ወደዚያ ስመለከት ፣ አይቼው የማላውቅ አስከፊው ጥቁር ጥላ ጉባኤው ላይ አጥልሎ አየሁ። አሁን መንፈስ ቅዱስ እዚህ አለ። አሁን በእኔ ላይ ነው። "መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን።"

ኢየሱስን መምሰል…

177 እሱ ምን አደረገ? አብ ወደመራው ሄደ። ጌታ ይባርክህ፡ ወንድም፣ ጌታ ይባርክህ፡ወንድሜ። ልክ ነው፤ ወደ ላይ እየወጣችሁ ተንበርከኩ።

በምድር ላይ ናፍቆቴ…

178 እንደ ድሮው-ጊዜ መናዘዝ፣ መታረም፣ መስተካከል፡ ጊዜው አሁን ነው። ኧረ። አሁንም ሌሎች እንዳላችሁ ይሰማኛል። ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት። ጌታ ይባርክሽ። ጌታ ይባርክህ። ጌታ ይባርክህ። ትክክል ነው። መንፈስ ቅዱስ ሁሌም ትክክል ነው። ተው'ጂ። ትክክል፣ ወጣ ወጣ በሉ።

… እሱን።

ኢየሱስን መምሰል፡ ኢየሱስን መምሰል፤
እኔ በምድር ላይ…

ኦህ፡ ማይ፡ ልክ ነው! ያ ነው መንገዱ፡ እየወጣችሁ መተላለፍያውን ሙሉት እና ጸልዩ።

በህይወት ጉዞ ከምድር ወደ ክብር፣

ንስሐ እየገባችሁ፣ እግዚአብሔር ይቅርታ በሉት፣ ያ ማድረግ ያለባችሁ።

… እሱን ለመምሰል።

179 አሁንስ መምጣታችሁን አትቀጥሉም?

ለ…

አዎን፡ ጥሳችሁ፡ ኑ።

… እሱን ለመምሰል…

180 ምንስ ታደርጋላችሁ? ማንስ ይቆምላችኋል፡ ምናልባት ዛሬ ማታ? ሞት እጅጌአችሁ ድረስ ሲጠጋ ማን ይቆምላችኋል? ምንም ብታደርጉ፡ መንፈስ ቅዱስ እዚያው በአጠገባችሁ ተቀምጧል። እንድትመጡ የሚፈልገው እሱ ነው።

በሕይወት ጉዞ ሁሉ ከምድር ወደ ክብር

181 ብቻ ንስሐ ግቡ፡ “ጌታ ሆይ ይቅርታ። ይሄን—ማድረግ አልፈልግም፡ በሉት። አሁን እኔ ካልቆምኩልህ አንተ ለእኔ አትቆምምና። አንተ እንትቆምልኝ እፈልጋለሁና፡ ከዛሬ ጀምሬ ስለ አንተ እቆማለሁ። ክርስትያን መኖር እንደሚገባው እኖራለሁ። አካሄደን እቀይራለሁ። ጨዋና የተረጋጋ እሆናለሁ። ሰዎች ወሬአቸውን፣ ሌላ ሁሉ ይበሉ እተዋቸዋለሁ። እኔ ግን በፊትህ ትሁት እና የተረጋጋ ህይወት እኖራለሁ።” ምንም ያህል ክርስቲያን ነኝ ብትሉ፡ የየትኛው ቤተክርስቲያን አባል ሁኑ፣ ምንም አይገናኝም። ጌታ ይባርክህ። ና ልጄ፡ ወደ ፊት ወጣ በል። አሁን ውጡ።

182 እግዚአብሔር አሁን ይናገራችኋል። የእርሱ አገልጋይ እንድሆን ካመናችሁኝ፣ መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ጠዋት ተናግሮኛል፣ “ብዙ ሰዎች ስለሚኖሩ፡ ያንን ጥሪ አድርግ፡” ብሎኛል። ዛሬ ነው ቀኑ፡ ጊዜው አሁን ነው። እዚያ ከኋላ አምስት ወይም ሰድሰት አላችሁ፣ በእርግጥ አሁን መምጣት አለባችሁ። አስታውሱ፡ ወንድም፡ እህት፡ ፊት ለፊት አያችኋለሁ፣ ጥቁር ጥላዎች በላያችሁ ተንጠልጥለው አያለሁ። ብትመጡ ይሻላል።

183 ኢየሱስን መምሰል! እንደ እርሱ፣ ጨዋ፣ የተርጋጋ፣ ገር፣ ትሁት መሆን አትፈልጉም? ጌታ ይባርክህ፡ ወጣት። እግዚአብሔር ይባርክህ አባት፡ ከህፃኑ ጋር። ጌታ ይባርክሽ እህት። ጌታ ይባርክህ፤ ኃጥያተኛው ወዳጄ። ትክክል። ወደ ላይ ውጪ፡ እህት፡ ነይ ቶሎ ውጪ፡ ጌታ ይባርክሽ፡ ለራስሽ ቦታ ፈልጊ።

184 እህቴ የተወደድሽ፡ የምታመሰግኚበት ብዙ ምክንያቶች አሉሽ። ለመሞት፡ አልጋ ቁራኛ የነበርሽ፡ ይሄው መሰውያው ጋር፡ ትራመጂያለሽ። ጌታ ይባርክሽ መልካም ልቧ።

185 መንፈስ ቅዱስ አሁንም ይናገራል። አብዝታችሁ በጌታ ፊት አልቅሱ፡ ንስሃ ግቡ፡ የራሳችሁን ጸሎት ብቻ ጸልዩ። ሐጥያት የሰራ እናንተ ራሳችሁ ስለሆናችሁ፡ የምትጸልዩም እናንተው ናችሁ። በዙርያችሁ ስላለው ሰው አትጨነቁ። ጌታን ስለሰራሁት ነገር ይቅር በለኝ በሉት። “አምላክ ሆይ፡ ይቅር በለኝ፡ እንዲህ ለመሆን ብየ አይደለሁም፡ በሉት። ጨዋ መሆን እፈልጋለሁ። ፈጽሜ መሰመር መጣስ—መታበይ አልፈልግም።”

186 አምላኬ ሆይ፣ ኦ፡ እንዴት እንደወደድኩት! የሰማይ አባት፣ ለእያንዳንዱ ንስሐ የገባ ሰው አሁን በመሠዊያው ላይ፣ በጉልበታቸው ተንበርክኮ፣ ለሚጸልዩ! አምላክ ሆይ፡ እናቶች፣ አባቶች፣ ልጆች፣ አባቶች፣ እናት፣ ሌላ፣ ጎረቤት፣ የቤተክርስቲያን አባላት፣ ዲያቆናት፣ ባለአደራዎች፡ ጌታ ሆይ፡ በዚህ-ጥንታዊ የመሰርያ-ጊዜ፣ ዛሬ ጠዋት በዚህ ሞቃት ክፍል ውስጥ ባለንበት፣ መንፈስ ቅዱስ ይምጣና፡ ሰላምን ይናገረን። ጌታ ሆይ፡ በዚያ ቀን በጨዋነት፡ እንዲህ ሰትናገር፡ መጽናት እፈልጋለሁ። “አዎ፡ አንተ መጥተህ ስለኔ መሰክረሃልና፣ አሁንም እኔ እመሰክርልሃለሁ።” ያንን ሰላም እዚህ ዛሬ ባለው ልብ ሁሉ ውስጥ እንድታሰቀምጥ፡ እፈልጋለሁ። በፀጥታ እና በእርጋታ፡ እንዲያደርገው እፈልጋለሁ። ከእንግዲህ ወዲያ፡ ፈጽሞ እንዳይተዋቸው በእንደዚህ ዓይነት ሰሜት ይዘው፡ ወደዚያ እንዲገቡ እፈልጋለሁ። ቤቶች ይታደሱ። ህዝቡም ይታደሱ ሰዎች ይሁኑ። እነዚህ ሰዎች እራሳቸውን ዝቅ ስላደረጉ፡ ዛሬ ሁሉም ነገር አዲስ ይሁን። አንተም እንዳልከው፡- “በሰሜ

የተጠሩት ሰዎች ራሳቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፣ ከዚያ ከሰማይ እሰማለሁ።” እና ዛሬ፡ ጌታ ሆይ፡ ይህን እንደሠራህ አውቃለሁ።

187 መምጣት ሲገባቸው፡ በወንበሮቻቸው ለቀሩት ሰዎችም ምሕረትን ኣለምናለሁ። እግዚአብሔር ሆይ፣ ተናገራቸው፡ ይህን ውሳኔ እስኪያደርጉ ድረስ በምድር ላይ ሰላም አይኑራቸው፣ ጌታየ፡ መጥተው ከአንተ ጋር እንዲታረቁ ነው። ይሁን፡ ጌታየ። አሁን እያንዳንዱን ባርክ። ዛሬ ጠዋት በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ በተፀፀተች እና ዝቅ ባለች ነፍስ ሁሉ ላይ ቸርነትህና ምህረትህ ለዘላለም ይኑር።

188 ጌታ አባት ሆይ፡ በትዕዛዝህ ይህን አድርጌአለሁ። እነዚህን ሰዎች ጠርቻቸው፡ ቆመዋል። “በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ፡ በአባቴና በቅዱሳን መላእክት ፊት እመሰክርለታለሁ፡” ብለሃል። እነዚህ ብዙዎቹ ለዓመታት ክርስቲያኖች ነበሩ፣ ነገር ግን ጥፋት እንደፈጸሙ ኃጢአታቸውን ለመታመን ዛሬ ጠዋት ቆመዋል። የማይወደዱ ሆነዋል። መንፈስ ቅዱስ ተለይቷቸዋል። እና ለብዙ ጊዜ ሊሰማቸው የሚገባውን ያንን ገር፣ ጣፋጭ፣ የዋህ ስሜት ሳይሰማቸው ቆይቷል። ብዙዎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጡ ኃጢአተኞች ናቸው። ግን፡ አባ፡ ያንን አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ አስደናቂው የሰላም ስሜት ይፈልጉታል። ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ሰጣቸው፡ ሁሉም የተወደዱ እና በመንፈስህ የተሞሉ ይሁኑ፡ ወደ ቤቶቻቸው ለመሄድ ዛሬ ከዚህ ቦታ ሲወጡ፣ የተለየ ሕይወት ለመኖር እና የተለየ ሕዝብ ለመሆን። ይህንን በክርስቶስ ስም እንጠይቃለን።

189 **ሩም አት ዘ ፋውንቴን።** መልካም፡ በመሰውያው ያላችሁ ሁላችሁ፡ ተነሱ፡ ጌታ አምላክን ተመልከቱት፡ በዙሪያዎ ካሉ ሰዎች ሁሉ ጋር ዘወር ብላችሁ እጆቻችሁ ተጨባበጡ። ኦህ፡ ከፈውስ አገልግሎቱ በፊት፡ ትንሽ ቆመን፡ ሁላችንም እንዘምራለን።

ክፍል ፣ ክፍል ፣ አዎ ፣ አለ፡ ክፍል፤
በምንጩ ላይ ለአንተ አለ ክፍል
ክፍል ፣ ክፍል ፣ አዎ ፣ አለ፡ ክፍል፤
በምንጩ ላይ ለአንተ አለ ክፍል።

ኦህ፡ ሁላችሁም!

... ቤት፣ አዎን፣ አለ፡ ቤት፤
በምንጩ ላይ ለአንተ አለ ክፍል፤
ኦህ፡ ቤት፣ ቤት፣ አዎን፣ ቤት አለ፡
በምንጩ ላይ ለአንተ አለ ክፍል።

ኦህ፡ ቤት፣ ቤት፣ አዎን፣ ቤት አለ!

190 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—ኤዲ.] ... ? ... እምነት! ወንድሜ፡ ሚስትህ በቀደም ለት—ስለ አንተ እንዲጸለይ፡ ሚስትህ ስትደውል ታስታውሳለህ? ወዲያው ወደ ክፍሉ ገባሁና፤ መንፈስ ቅዱስ “አትፍራ” አለኝ። አሜን። እሱ እውን አይደለምን? ድንቅ! እንግዲህ፣ ጌታን አመስግኑ! ድል ብየ እንድጮህ ይሰማኛል! በጣም ጥሩ።

ደሙ አጥርቶ ያጥባል...

(ማለት የምትፈልገው አለ? )

(ኢየሱስ ያድናል!)... ? ...

191 መልካም፣ አሁን ወደ ወንድም ኔቪል። ወንድም ስላውተርም የሚናገረው ቃል አለው።

[ወንድም ስላውተር ተናገረ። በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]

192 [ወንድም ኔቪል እንዲህ አለ፦ "ማይ! ጌታ ይመስገን! አሜን! እግዚአብሄር ይመስገን! ዛሬ ጠዋት ሰው ሁሉ እንደተባረከ እምናለሁ።"—አርታዒ።] ክብር! ሃሌ ሉያ! ሃሌ ሉያ! ["ዛሬ ሁላችንም አሁን እግዚአብሔርን እንደተቀበሉ መሰለናል። ሃሌሉያ! እዚህ መድረክ ላይ ያለውን መልካም በረከት እና ቅባት ይሰማችሁ፡ እንደ ጴጥሮስ ይሰማችሁ፡ እርሱ፡ ለራሴ አላለም... ? ... ሦስት ድንኳኖች እንስራ፡ እና እዚሁ እንቆይ። አሜን። ልዩ ነው። ሰው ሁሉ ተባርኳል።"]

193 ["አሁን ሁላችሁ በእግሮቻችሁ ቁሙ። አሜን። የዛሬ ማታ ጉባኤ አስታውሱ፡ እግር-መታጠብ እና የጌታ እራት አለ። (መቼ መምጣት እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ? )"] ዛሬም፡ ምናልባት እመጣለሁ ብዬ እገምታለሁ። ["ምናልባት ዛሬ ምሽትም እገኝ ይሆናል።"] አዎን፡ እስከማውቀው ድረስ፡ ወደ ሌላ ቦታ ካልተጠራሁ በቀር እመጣለሁ። ["አሜን"]

**ቤተክርስትያን እና ሁኔታዋ** AMH56-0805

(The Church And Its Condition)

**የቤተክርስትያኒቱ መተካካት**

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ በ የተላለፈ መልዕክት እሁድ ማለዳ፥ ነሐሴ 5፡1956፡ በብራንሃም ተበርናክል በጀፈርሰንቪል ኢንዲያና፡ U.S.A. ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰደ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2021 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org